# መማርና ማደግ

## ክርስቲያናዊ ትምህርት

ከኢንተርናሽናል ኮርስፖንዳንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር
በድዌይን ተርነር ተዘጋጅቶ በሥነ መለኮት በቤቴ አማካኝነት
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተመለሰ የክርስቲያናዊ ትምህርት
መማሪያ መጽሐፍ

**Helping Others Grow**
**A Study of Christian Education**

**ሁለተኛ ዕትም**
**ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው**

**ሥነ መለኮት በቤቴ**
2002 አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ ............................................................ 3

ሕያውነትና ዕድገት ............................................. 7

ወደ ብስለት ማምራት ......................................... 26

ክርስቲያኖች እንዲያድጉ መርዳት ......................... 43

ማወቅና ማድረግ ................................................. 66

ማደግና መማር .................................................. 87

ተማሪ አስተማሪውን ይመስላል .............................. 117

ሰዎች እንዲማሩ መርዳት ...................................... 138

በቤተሰብ ውስጥ ማደግ ......................................... 157

በአነስተና የኅብረት ቡድን ውስጥ ማደግ ..................... 175

በቤተ ክርስቲያን ማደግ ........................................ 198

የሙከራ ፈተና መልሶች ........................................ 217

## መግቢያ

"ቤተ ክርስትያን የትምህርት ፕሮግራም እንዲኖራት ለምን አስፈለገ?" ወይም "ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን ዓላማ ጋር በምን መልኩ ይጣመዳል?" በማለት ጠይቀህ ሊሆን ይችላል። ክርስቲያናዊ ምግባ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጣም አስፈላጊ ነው ። የትምህርት አገልግሎት በክርስትና ዕምነት ለማደግና ለመብሰል ይጠቅማል። ሌሎችን ለመድረስ በምናደርገው ጥረት እንድንዘጋጅና እንድንሰለጥን ይረዳናል። ይህንን ኮርስ ማጥናትህ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንድታድግና የበለጠ ክርስቲያናዊ ትምህርት እንደሚያስፈልግህ እንድታይ ይረዳሃል። ሌሎችንም ስለ ክርስትና ዕምነት ለማስተማር በምታገኘው አጋጣሚና ዕድል እንድትሳተፍ ሊያስለጥንህና ትጥቅ ሊሆንህ ይችላል።

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ዕምነትንም ሆነ ተግባርን ሁሉ በተመለከተ ከፍተኛው ባለሥልጣን እንደሆነ ይገነዘባሉ። አገልግሎታቸውንም ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚያገኙት እሳቤዎችና መርሆዎች ላይ ይመሠርታሉ። በዚህ ኮርስ ውስጥ በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የቀረበውንና ስለመማርና ማስተማር የተሰጠውን ተግባራዊ ትምህርቶች በማጥናት ስለ ክርስቲያናዊ ምግባ የተሻለ መረዳት ታገኛለህ።

በሥራ ላይ የሚውለው የማስተማር ዘዴ ከቦታ ወደ ቦታ ሊለያይ ይችላል። እኔ ያለሁበት ቦታ የምንጠቀምበት የማስተማር ዘዴ በአንተ አካባቢ ጥቅም ላይ ከሚውለው ይለይ ይሆናል። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎታችንን የምንመራበት ሠፋ ያለ መሠረት ያለው መርሆዎችን ይሰጠናል። ከዚህም የተነሳ እነዚህን መርሆዎች እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ ዘዴዎች ውስጥ ልንጠቀምባቸው እንችላለን ። ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ባሕሪና ክርስቲያናዊ ዕድገት መርሆዎች ስንነጋገር፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገታችን የሚሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችንና የሰዎችን መንፈሳዊ ፍላጎት ለመመለስ እነዚህን መመሪያዎች እንዴት በተግባር እንደምናውል እንመለከታለን።

*መማርና ማደግ፡ ክርስቲያናዊ ትምህርት* የተባለው ይህ ትምህርት የምግባ አገልግሎትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ማስተማር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚውል የሚያሳየን ትምህርት ነው ። በተለያየ የዕድሜ እርከን ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን ፍላጎት በትኩረት ከማመልከቱም በላይ፤ በእጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ በአነስተኛ ቡድንና በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ክርስቲያናዊ ምግባን እንዴት መፈጸም እንደሚቻል በሠፊው ያስተምርሃል።





## የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

1. ለክርስቲያናዊ ምግባ አስፈላጊነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶችን ማቅረብ፤
2. ክርስቲያናዊ ምግባ ከመማርና ማስተማር ጽንሰ ሐሳብና ሂደት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማስረዳት፤
3. የሌሎችን መንፈሳዊ ሕይወት ለመመገብ የቀረበልህን ዕድል መገንዘብና ማጠቀም፤
4. ምግባን ከተፈጥሮአዊና መንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ጋር ማዛመድ፤
5. በተማሪና በአስተማሪ መካከል ባለው ግንኙነት የክርስቲያናዊ ምግባን አስፈላጊነትና ውጤት ማወቅ፤
6. ክርስቲያናዊ ምግባ በቤተሰብ ግንኙነት ውስጥ ያለውን ሚና ማስረዳት።

## የትምህርቱ አዘገጃጀትና የአጠናኑ ስልት

እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ይይዛል።

1. ርዕስ
2. መግቢያ
3. የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
4. የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች
5. የትምህርቱ ዝርዝር
6. ለጥናቱ የሚረዱ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች
7. የሙከራ ፈተና (ከትምህርቱ በበተመጨረሻ)
8. የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስና በመጽሐፉ መጨረሻም የሙከራ ፈተናዎች መልስ ቀርበዋል።

የትምህርቱ አከፋፈልና ዓላማዎች በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ሃሳብ ይሰጣሉ፤ ጥናቱን በምታጠናበት ወቅት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ነጥቦች ላይ እንድታተኩር ይረዱሃል።

በትምህርቱ ዝርዝር ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በዚህ የጥናት መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ክፍት ሥፍራዎችን በመሙላት ሊመለሱ የሚችሉ ናቸው። ሆኖም ረዘም ያሉ መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ መጻፍ ይገባል። መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ የምትጽፍ ከሆነ የጥናቱን ቁጥርና ርዕሱን መመዝገብህን እርግጠኛ ሁን።

የራስህን መልሶች ከመስጠትህ በፊት በመጽሐፉ የቀረቡትን መልሶች እትመልከት። የራስህን መልሶች የምትበጥ ከሆነ ያጠናኸውን ጥናት በተሻለ ሁኔታ ትረዳዋለህ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን ከመለስህ በኋላ በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ። ከዚያ በኋላም በትክክል ያልመለስካቸውን አርማቸው። የቀረቡትን መልሶች በድንገት ተመልክተህ የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት እንዳትችል መልሶቹ የቀረቡት በቁጥር ቅደም ተከተል አይደለም። እነዚህ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በጥናቱ የቀረቡትን ዋና ዋና ሃሳቦች እንድታስታውስ ከመርዳቱም በላይ ከትምህርቱ ያገኘሃቸውን የሕይወት መርሆዎች ተግባራዊ እንድታደርግ ይረዳሃል።





# 1 ሕያውነትና እድገት

## ትምህርት

ገርማና ፀሐይ አዲስ በተወለደው ሕፃን በጣም ተደስተዋል። የልጁም መወለድ ለቤታቸው ትልቅ ደስታን አምጥቷል። እናም አሁን እያጣጣሙ ያለውን ሕይወት በቃላት ሊገልጹት አይችሉም። ይሁን እንጂ በትከሻቸው ላይ ያረፈውን ኀላፊነት ቀስ በቀስ እየተረዱት መጥተዋል። የሕፃኑ ሕልውና የተመሠረተው በእነርሱ ላይ ነው፤ ማለትም ሕፃኑ በሕይወት ሊኖር የሚችለው የሚያስፈልገውን ሁሉ ሲያዘጋጁለትና በአግባቡ ሲንከባከቡት ብቻ ነው።

የተወለደው ሕፃን እንደምን ፈጥኖ አደገ! ፀሐይ የሕፃኑን እድገት ልብ ብላ ታያለች። በየዕለቱ ቁመቱና ሰውነቱ እየጨመረ ነው፤ ሕፃኑ የተወለደው ኀላፊነታቸውን በትክክል ከሚያውቁና ለልጃቸውም የሚያስፈልገውን ከብካቤ ከሚያደርጉ ወላጆች በመሆኑ በየቀኑ እያደገ ነው።

ሳምንቱ በወር፥ ወሩ በዓመት እየተተካ በሄደ ቁጥር፥ ሕፃኑም ጊዜውንና ወቅቱን ጠብቆ ሊያድግ እንደሚችል እንገምታለን። ከዓመታት በኋላ ሕፃኑ ከምን ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል መገመት ለፀሐይ ከባድ አይደለም። ምክንያቱም ሕፃኑ ሕያው ነው፤ ሕያው በመሆኑ ያድጋል።

ልክ እንዲሁ፥ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ብስለት መታየት አለበት። በዚህ ትምህርት ውስጥ መንፈሳዊ እድገት እንዲኖር ከተፈለገ፥ መንፈሳዊ ሕይወትን መመገብ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን እንመለከታለን፤ ከዚህ በተጨማሪ መንፈሳዊ እድገት እንዲኖር ምን መመገብ እንዳለብን እንማራለን።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የመንፈሳዊ እድገት ጠባይ
- መመገብና መንፈሳዊ እድገት
- ለመንፈሳዊ እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ክርስቶስን እንድንመስል ኀይል ይሰጠናል (ቆላ. 1፥27)። አሁን የክርስቶስ መንፈስ በአንተ ውስጥ ይኖራል፤ ሕይወትህንም ይቆጣጠራል። የሕይወትህ ጌታ እንደመሆኑ፥ የሕይወትህ ጌታ እንዲሆን በፈቀድህለት መጠን ሕይወቱን በአንተ ሕይወት ይገልጣል (ሮሜ 6፥9–10)።

እስቲ አሁን ገና አዲስ ስለተወለደ ሕፃን አስብ። ይህ ሕፃን ወደፊት ምን እንደሚሆን ማን ያውቃል? ሕፃኑ ማደግና መጎልበት የሚያስፈልገው አካል አለው። ይህ ሕፃን ተገቢ ክብካቤ፥ የተመጣጠነ ምግብ፥ የተስተካከለ መኖሪያ፥ ተገቢ ድጋፍና ልዩ መብት ከተሰጠው ሙሉና በነገር ሁሉ የበሰለ ሰው ወደ መሆን ደረጃ ይደርሳል። ሕፃኑ ወደፊት ሙሉ ሰው ለመሆን የሚያስችለውን ነገር ሁሉ በውስጡ ይዟል፤ ሆኖም እነዚህ ነገሮች በተገቢው መንገድ ማደግ የሚገባቸው ነገሮች ናቸው።

ይህን ገና አዲስ በተወለደ ሕፃን ላይ የምናየውን ዕድገት ወደ መንፈሳዊው ዓለም አምጥተን በመንፈሳዊ ሕይወት መብሰል ከሚለው ሐሳብ ጋር ልናስተያየው እንችላለን። ጌታ እያንዳንዳችን የተትረፈረፈ ሕይወት እንድናገኝ ይፈልጋል። ታዲያ አንድ ሰው የተትረፈረፈ ሕይወት የሚያገኘው እንዴት ነው? ከፍ ሲል እንዳመለከትነው፥ አዲስ ልደት ባገኘህ ጊዜ (ዳግም በተወለድህ ጊዜ) አዲስ ሕይወት መኖር ጀምረሃል። እንደ መንፈሳዊ ሕፃን መኖር ጀምረሃል፤ ደግሞም በክርስቶስ ሕፃን ሆነህ መኖር ጀምረሃል። በሁሉ ነገር ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል። ሆኖም ገና ሙሉ በሙሉ አላደግህም። የተትረፈረፈውን አዲሱን ሕይወት ለማግኘት በመንፈሳዊ ሕይወት መብሰልና መጎልበት ያስፈልጋል።

ባጠቃላይ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሊሆን በመንፈስ ማደግ ይጀምራል። ይህ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሲሆን በሕይወቱ ለማደግ ዝግጁ ነው፤ ሆኖም መንፈሳዊ ምግብ ያስፈልገዋል። በሕይወቱ ማደግ ሲጀምር የተሰጠውን አስደናቂ ዕድል ብቻ ሳይሆን የተሰጠውንም ኀላፊነት ማስተዋል ይጀምራል። የእግዚአብሔርን ቃል እያወቀ ሲመጣ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ያለውም መረዳት በዚያው መጠን እያደገ ይሄዳል። ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሲሆንና በየዕለቱም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሲራመድ በሕይወቱ ውስጥ የእግዚአብሔር ሐሳብ ምን እንደሆነ የበለጠ ግልጽ እየሆነለት ይመጣል (ገላ. 5፥25)። ከዚህ ቀጥለን እንደምንመለከተው፥ ሥጋዊ ሕይወታችን ምግብና ክብካቤ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በሕይወታችንም ውስጥ የተዘራው መንፈሳዊ ዘር እንዲበስልና እንዲያፈራ ምግብና ክብካቤ ያስፈልገዋል።

(1). «እውነት» የሆነውን ዐረፍተ ነገር አክብብ።

ሀ. አንድ ሰው አዲስ ሕይወትን ሲያገኝ ወዲያውኑ ፍጹምና በነገር ሁሉ የበሰለ ሰው ሆኖ እንደሚያድግ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ፤ በሌላ አነጋገር እንዲህ ያለውን ሕይወት ያገኘ ሰው ማደግና መብሰል አይጠበቅበትም።





ለ. የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ደረጃዎች እንደሌሉ ኢየሱስ አስተምሯል፤ ስለዚህ አንድ ሰው አዲስ ሕይወትን ሲያገኝ ወዲያውኑ የተትረ ፈረፈ ሕይወትን ይቀበላል።
ሐ. ጌታ የተትረፈረፈ መንፈሳዊ ሕይወትን እንዳዘጋጀልን ቅዱሳት መጻሕ ፍት ያስተምራሉ፤ ይሁን እንጂ ይህ ሕይወት በዕድገትና በብስለት ሕግ የተገዛ ነው።
መ. አንድ ሰው የኢየሱስ መንፈስ ሕይወቱን እንዲቆጣጠርና እንዲመራ ሲያደርግ በዕድገት ሂደት ላይ ነው።
ሠ. አዲስ ሕይወትን የተቀበለ አዲስ ክርስቲያን መንፈሳዊ ምግብ ሲመገብ፥ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ተስማሚ የሆነ ሁኔታ ሲመቻችለትና መንፈስ ቅዱስ በሚመራው አቅጣጫ ለመሄድ ሕይወቱን አሳልፎ ሲሰጥ እያደገና እየበሰለ ይሄዳል።

## የመንፈሳዊ ዕድገት አስፈላጊነት

*ዓላማ 2 በዚህ መጽሐፍ ላይ በዝርዝር እንደተጠቀሰው ስለ መንፈሳዊ ዕድገት አስፈላጊነት የተሰጠውን ትክክለኛ ትርጉም መረዳት።*

ለቶ የማያድግ ሕፃን ምን እንደሚመስል አስበህ ታውቃለህ? ብዙ ዘመን የኖረ ነገር ግን አሁንም ሕፃን የሆነና ምንም ያላደገ ሰው አይተህ ታውቃለህ? እንዲህ ዐይነት ሰው ብታይ ወዲያውኑ ይህ ሰው አንድ ችግር አለበት ትላለህ። እንዲህ የምትለው አንድ ሕፃን ከተወለደ በኋላ በየጊዜው ማደግና መብሰል እንዳለበት ስለምታስብ ነው። ሕይወት ያለውና ጤናማ የሆነ ሰው ሁሉ ያድጋል፤ ይበስላል።

ኢየሱስ የመንፈሳዊ ዕድገት መርሆችን ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮአል። መንፈሳዊ ሕይወትን ከወይን ግንድና ከቅርንጫፍ ጋር በማነጻጸር በግንዱ ላይ ያለ ቅርንጫፍ ከግንዱ ተለይቶ ሊያድግና ሊያፈራ እንደማይችል አስረድቶአል። በወይኑ ግንድ ላይ የሚገኙ ቅርንጫፎች ከወይኑ ግንድ ጋር ፍጹም መጣበቅ አለባቸው። ምክንያቱም ቅርንጫፍ የሚያድገውና ፍሬ የሚያፈራው ከግንዱ ጋር ሲጣበቅ ብቻ ነው። ልክ እንዲሁ ከእውነተኛው የወይን ግንድ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ፍጹም ያልተጣበቀ ክርስቲያን መብሰልና መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት ከቶ አይችልም (ዮሐ. 16፥1–16፤ ቁ. 4፥ 5፥ 8 እና 16 ልብ ብለህ ተመልከት)። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የማያድግና የማይበስል ክርስቲያን የሚጠብቀው ነገር ቢኖር መንፈሳዊ መበስበስ፥ መድረቅና በመጨረሻም መንፈሳዊ ሞት ነው (ዮሐ. 16፥2–6)።

አንድ ሕፃን ልጅ በአንድ ቀን እንደማያድግ ጠንቅቀን እናውቃለን። ዕድገትና ብስለት ጊዜ የሚፈልጉ ነገሮች ናቸው። በመንፈሳዊ ሕይወትም ዕድገት የሚመጣው በዚሁ የዕድገት ሕግ መሠረት ነው። ዕድገታችንን እንደ ሕፃን ብንጀምርም፥ ውሎ አድሮ ግን ዕድገትና ብስለት ይመጣል። አንድ ሕፃን ወደ ጉልምስና (ሙሉ ሰው ወደ መሆን) እንደሚያድግ ሁሉ፥ በክርስቶስ ሕፃን የሆነ ሰው እንዲሁ ወደ መንፈሳዊ ብስለት ያድጋል። ይህ ዕድገት ይኖራል

ብለን የምናምነው፥ ሰውየው በመንፈስ ሕያው በመሆኑ ነው። ከመንፈስ ሕያው የሆነ ሰው በትክክል እስከተመገበና በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር እስከሆነ ድረስ ያድጋል፤ ይበስላል። ያን ጊዜ ብቻ ነው አንድ ሰው እግዚአብሔር የጠራውን መንፈሳዊ ዓላማ ፈጸመ ማለት የሚቻለው። ያን ጊዜ አብ በሕይወቱ እንዲያፈራው የሚፈልገውን ዘላለማዊ ፍሬ ማፍራትና (ዮሐ. 15፥16) እግዚአብሔር በዚህ ምድር እንዲፈጽመው የሚሻውን ሥራ ማከናወን ይችላል።

2–3 ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት መልሶች ውስጥ «እውነት» የሆነውን ዐረፍተ ነገር አክብብ።

(2). ሕያው የሆነ ሕይወት

ሀ. ሕፃን እንደሆነ ይቀራል።
ለ. እያደገና እየበሰለ ይሄዳል።
ሐ. ባንድ ጊዜ ያድጋል።
መ. ለውጥ የሚታይበት ከሆነ ትንሽ ፍሬ ያፈራል።

(3). መንፈሳዊ ዕድገት እንዲኖር ጌታ ኢየሱስ ስላዘዘ አዲስ ሕይወት የተቀበሉ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ አለባቸው፤ ምክንያቱም (ትክክለኛ የምትለውን መልስ ምረጥ)።

ሀ. አዲስ ሕይወት ባገኘን ጊዜ ወዲያውኑ ፍጹምና ሙሉ ሰው እንሆናለን።
ለ. አንድ ሰው የተቀበለውን መንፈሳዊ ስጦታ ማሳደግ እጅግ አስቸጋሪ ነው።
ሐ. በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ ሰው የጌታን ፈቃድ ይፈጽማል፤ ደግሞም የጌታን ሥራ ውጤታማ በሆነ መንገድ ያከናውናል።

## መመገብና መንፈሳዊ ዕድገት

*ዓላማ 3 መንፈሳዊ ሰው ለምን መመገብ እንዳለበት የሚገልጹትን ዐረፍተ ነገሮች ምረጥ።*

ልጅ የወለደች እናት ልጅዋ በሕይወት እንዲኖርና እንዲያድግ ከፈለገች ሕይወቱ መመገብ እንዳለበት ታውቃለች። አንድ አዲስ የተወለደ ሕፃን በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያገኘው ከሌሎች ነው። አዲስ የተወለዱ ሕፃናት ሁሉ የሌሎች ጥገኞች ናቸው። በመሆኑም እናቶች ለልጆቻቸው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በማዘጋጀት ልጆቻቸውን በፍቅር ይከባከባሉ። እንዲህ ያለ ክብካቤ የማይደረግላቸው ሕፃናት ቶሎ ይሞታሉ። አዲስ የተወለዱ ሕፃናት ራሳቸውን በራሳቸው መመገብ የማይችሉ በመሆናቸው የሌሎችን ዕርዳታ በእጅጉ ይሻሉ።

ልክ እንዲሁ መንፈሳዊ ሕይወትም መመገብ አለበት። አንድ ሰው መንፈሳዊ ልደትን እንዲያገኝ መርዳት ለዚያ ሰው የምንሰጠው የመጀመሪያ ክርስቲያናዊ





ኀላፊነት ነው። ሰውየው አዲስ ልደት ካገኘ በኋላ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲሰነብትና እንዲበስል መንፈሳዊ ሕይወቱን መመገብ አለብን። በመንፈስ ሕፃናት የሆኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ቢሆኑም፥ መንፈሳዊ ስጦታቸውን ገና ማሳደግ ጀመሩ እንጂ ጌታ እንደሚፈልገው የተትረፈረፈ መንፈሳዊ ሕይወት ገና አላገኙም። በመንፈሳዊ ሕይወት ሕፃናት የሆኑ ሰዎች መንፈሳዊ ምክርና ዕርዳታ የሚሰጧቸውን ወንድሞችና እኅቶች ይሻሉ። እንዲህ ያለ ምክርና ዕርዳታ የሚያገኙ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉና እየበሰሉ ይሄዳሉ። እንግዲህ አዲስ አማኞች ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወት ለመኖርና ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት ለማደግ መንፈሳዊ ሕይወታቸው መመገብ አለበት።

አዲስ ሕይወት በአግባቡ ከተመገበ፥ ብስለት እንደሚኖር እሙን ነው። እንዲህ ያለውን ዕድገት በአትክልት በእንስሳት በሕፃናት ወይም በአዲስ አማኝ ሕይወት ላይ ማየት ይቻላል። የመመገብ አገልግሎት አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ወደ ሙሉ ብስለት የሚያድግበትን መንገድ ያመቻቻል።

እዚህ ላይ ጴጥሮስ ለላለው አገልግሎት ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ታስታውስ ይሆናል። መንፈሳዊ ሕይወትን የመመገብ ተልዕኮ በተለያየ ክርስቲያናዊ ብስለት ደረጃ ላይ ያሉትን ሁሉ ያካትታል፤ ከግልገል እስከ በግ ድረስ ያሉትን (ዮሐ. 21፥15–17 ተመልከት)። ጴጥሮስ በተለያየ የብስለት ደረጃ ላይ ያሉትን ሁሉ መመገብ አስፈላጊ መሆኑን ከተረዳ በኋላ መላውን መንጋ እንዲጠብቅ ጌታ የሰጠውን ትእዛዝ በሙሉ ልብ ተቀበለ፤ በመልእክቱም ላይ ሕፃናት ስለሆኑትና (1ጴጥ. 2፥2) ስለ ጠቅላላው መንጋ ጠቅሶአል (1ጴጥ. 5፥1–4)። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ክርስቲያን አገልጋዮች በዚሁ መሠረት መንፈሳዊ ሕይወትን እንዲመግቡ መክሮአል፤ ጴጥሮስ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድገውና ወደ ታላቀለትም ደረጃ የሚደርሰው በአግባቡ ሲመገብ እንደሆነ ያውቃል።

(4). «እውነት የሆነውን ዐረፍተ ነገር አክብብ።

ሀ. መንፈሳዊ ሕይወት የዕድገትና የብስለት የመጨረሻው ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ ፈተናን መቋቋም አይችልም።
ለ. መንፈሳዊ ሕይወት በሕፃንነት ደረጃ ላይ ብዙ ጥንካሬ ስለ ሌለው እስኪጠነክርና እስኪበለል ድረስ የክርስቲያን ወንድሞችን እርዳታ ይሻል።
ሐ. መንፈሳዊ ሕይወት በክርስቲያናዊ ምግባ በመታገዝ ሊያድግ ይችላል።
መ. መንፈሳዊ ሕይወትን ለንመግብ፥ ለመንፈሳዊ ዕድገት ተስማሚ የሆኑ ሁኔታዎችን ልናመቻች እንችላለን፤ ሆኖም ድካማችን ፍሬ ያፍራ ወይም አያፍራ አስቀድመን መናገር አንችልም።

ችሎታ የተለያየ ነው። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ያለው ችሎታ በየትኛው የብስለት ደረጃ ላይ እንዳለ ያሳያል። «የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለበት ሰው» መንፈሳዊ ምግብን መረዳት ወይም መመገብ አይችልም፤ ይህ ሰው የሚፈልገው ሌላ ነገር ነው። ባንጻሩም «ሥጋዊ ሰው» መንፈሳዊ ሕፃን ነው። ይህ ሰው መመገብ ያለበት መንፈሳዊ ወተት ብቻ ነው። ምክንያቱም ይህ ሰው የሚረዳው ቀላል መንፈሳዊ እውነቶችን ብቻ ነው። ሁልጊዜ የሚፈልገው የጌታን በረከት መቀበልና ደስ መሰኘት ብቻ ነው። ነገር ግን ለመንፈሳዊ ጉልምስና ያለው አመለካከት በጣም ጠባብ ነው። በመሆኑም መንፈሳዊ ሰው ለመሆንና መንፈሳዊ ጡንቻዎቹንም ለማሳደግ ምንም ፍላጎት የለውም። አሁኑኑ ተነሥቶ ራሱን ማዘጋጀት ሲችል፥ ነገ ይሄን አደርጋለሁ ነገ ያንን አደርጋለሁ እያለ የነገ ሰው ሆኖ ይቀራል። «መንፈሳዊ ሰው» ግን ራሱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ ስጥቶ ስለሚኖር፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረት ዘወትር እየጠነከረ ይሄዳል። ሁልጊዜ ለማግኘት የሚፈልገው ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችንና የእግዚአብሔርን ቃል ጠንካራ ምግብና ሥጋ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የተረዳውን እውነት ለሌሎች ያካፍላል፤ በመንፈሳዊ ብስለት ከእርሱ በታች የሆኑ ሰዎችን ያበረታታል፤ በክርስቶስ አካል ውስጥ ፍሬያማ የሆነ አገልግሎትና ትምህርት ይሰጣል።

ጳውሎስ የመንፈሳዊነት ደረጃዎችን አስመልክቶ የሰጠን ትምህርት የሚያሳየን፥ የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያመጣ መንፈሳዊ ምግብ መሆኑን ነው። አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠው ቦታ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጤናማና ፍሬያማ ሆኖ እንዲበስል አልያም ዝንተ ዓለሙን መንፈሳዊ ሕፃን ሆኖ እንዲቀር ያደርገዋል፤ መንፈሳዊ ሕፃን ሆኖ የቀረ ሰው ደግሞ ለከፋ ነገር የተጋለጠ ነው።

(6). በስተግራ በኩል የተጠቀሱትን ባሕርያት በስተቀኝ በኩል ከተሰጡት የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃዎች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ____ ሀ. ደስ ሲለውና ሲሰማው ብቻ መንፈሳዊ ይሆናል እንጂ፤ መንፈሳዊ ኃላፊነቱን አልተገነዘበም። | 1. የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው ሰው |
| ____ ለ. መንፈሳዊ ነገርን ጨርሶ አይረዳም፤ አያስተውልም። | 2. ሥጋዊ ሰው |
| ____ ሐ. የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ለመረዳት ከልብ ይፈልጋል፤ ሚዛናዊ ፍርድ ይሰጣል የተረዳውን እውነት ለሌሎች ያካፍላል። | 3. መንፈሳዊ ሰው |
| መ. አዲስ ልደት አላገኘም። | |
| ____ ሠ. አዲስ ልደት/ሕይወት አግኝቷል፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ሕፃን ሆኖ ቀርቷል። | |
| ረ. ከመንፈሳዊ ሕፃንነት ወደ መንፈሳዊ ብስለት እያደገ ይሄዳል። | |





# የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ

*ዓላማ 6 መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ዕድገትን እንዴት እንደሚያመጣ የሚገልጹ ዐረፍተ ነገሮችን ምረጥ።*

ስለ መንፈሳዊ ዕድገት ደረጃዎች ስንነጋገር፥ የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያመጣ መንፈሳዊ ምግብ መሆኑን ተወያይተናል። የአንድ ሰው መንፈሳዊ ዕድገት ለእግዚአብሔር ቃል በሚሰጠው ቦታ የተወሰነ መሆኑንም ተነጋግረናል። አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ዕድገትን እንዴት እንደሚያመጣ ጠለቅ ብለን እንመርምር።

ይህ የምናየው ዓለም ስለ ፈጣሪያችን ስለ እግዚአብሔር ብዙ የሚያስተምረን ነገር ቢኖርም ይህ መገለጥ ግን ጥቅልና ከፊል ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ራሱን የበለጠ ገልጦልናል። ይህ የምናየው ዓለም የእግዚአብሔርን ኀያልነትና ጠቢብነት ሲገልጥልን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ቅድስናውን፥ ዳኝነቱን፥ እውነቱን፥ ምሕረቱንና ፍቅሩን ይገልጥልናል። ከዚህ በተጨማሪ ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ባሕርይ፥ ሐሳብና ፈቃድ ገልጠውልናል። በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ማንነቱን አስታወቀን።

የእግዚአብሔር ቃል፥ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያሰውን ሐሳብ ያስታውቀናል። እርሱን ደስ የሚያሰኘው አገልግሎት እንዴት ያለ እንደሆነ፥ ከእርሱ ጋር ያለን ኅብረት እየጠነከረ እንዳይሄድ የሚያደርገውን ስሕተት እንዴት ማረም እንደምንችል፥ መንፈሳዊ ሕይወት ምን እንደሆነ፥ መንፈሳዊ ድል እንዴት ማግኘት እንደምንችል፥ የክርስቲያን ሕይወት ግብ ምን እንደሆነ ያስተምረናል። ባጭሩ መጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ሕይወት ካርታ ነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ ቀስቃሽነት የተጻፉና ሕይወት ሰጪ በመሆናቸው መንፈሳዊ ዕድገትን ያስገኛሉ። በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የሚኖረው መንፈሳዊ ሕይወት በክርስቲያኖችም ላይ ይኖራል። በቃሉ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሕይወት እግዚአብሔር ለሚሰጠው አዲስ ሕይወት ምንጭ ነው። በውስጣችን ያለው መንፈሳዊ ሕይወት ከቃሉ ውስጥ ለሚፈሰው መንፈሳዊ ምግብ መልስ ይሰጣል። ቃሉ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ተስማሚ ምግብ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር ያሰበውን ነገር በሕይወታችን እንዲፈጽም ፈቃደኞች መሆን አለብን። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ስንፈልግ፥ ክርስቶስን እየመሰልን እናድጋለን (2ቆሮ. 3፥18)።

(7). መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወትን እንዴት እንደሚመግብ (መጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ሕይወት እንዴት ምግብ ሊሆን እንደሚችል) የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር አክብብ።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወትን ለማቆየትና ለማሳደግ የሚረዳንን ምግብ ይሰጠናል።

ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲ ያውቅና ላወቀው እውነት ምላሽ እንዲሰጥ ይረዳዋል።
ሐ. በቃሉ ውስጥ የሚገኘው የእግዚአብሔር ሕይወት በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ከሚገኘው የእግዚአብሔር ሕይወት ጋር ዝምድና/ ጥምረት አለው፤ ስለዚህ አንድ አማኝ ቃሉ እንዲለውጠው ራሱን ሲሰጥ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዐይነት ሰው እየሆነ ይሄዳል።
መ. አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስተምረውን እውነት ሲያውቁ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጋሉ።

## በእርስ በርስ ግንኙነት መመገብ

*ዓላማ 7 የእርስ በርስ ግንኙነት መንፈሳዊ ዕድገትን እንዴት እንደሚያመጣ የሚገልጹትን ዐረፍተ ነገሮች ምረጥ።*

አንድ ሕፃን ቢወለድ የቤተሰቡ አባል ይሆናል። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ለሕፃኑ ቦታ መስጠትና ለሕፃኑም የሚያስፈልገውን ነገር ያደርጋል። ለአዲሱ ሕፃን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ቤተሰቡ ይተባበራል። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ለሕፃኑ የሚያስፈልገውን ነገር ለማዘጋጀትና የሕፃኑን ሕይወት ለማሳደግ ራሱን ይሰጣል። ሕፃኑ በሚያድግበት ጊዜ ሁሉ ቤተሰቡ በሙሉ ለሕፃኑ የሚያስፈልገውን ነገር ያዘጋጃል፤ ሕፃኑን ይከባከባል። አንዱ ለሌላው ማካፈል፥ አንዱ ሌላውን መንከባከብና እርስ በርስ መደጋገፍ በማንኛውም ቤተሰብ ውስጥ የማይታጣ ባሕርይ ነው። በቤተሰቡ መካከል የሚታየው የእርስ በርስ ግንኙነት ጥንካሬ በቤተሰቡ ውስጥ ለሚጨመረው አዲስ ሕይወት ወሳኝ ነው።
በመንፈሳዊ ሕይወትም ልክ እንዲሁ ነው። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የምናደርገው ኅብረት ለመንፈሳዊ ዕድገት ዐይነተኛ አስተዋጽዖ አለው። በአማኞች መካከል የሚደረግ ኅብረት ለመንፈሳዊ ዕድገት መሠረት ነው።

አንድ አዲስ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ነገር በጣም ከበሰለ ሰው ጋር የጠበቀ ኅብረት ቢኖረው መልካም ነው። የበሰለው ክርስቲያን እንደ መንፈሳዊ አባት ሆኖ አዲሱን ክርስቲያን በፍቅር እየተንከባከበ ያሳድጋል። እንደዚህ ዐይነቱ ሰው አዲሱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠናና ከሕይወቱ ጋር እንዲያዛምድ ሲረዳው ይችላል፤ ደግሞም ምሳሌያዊ ሕይወት በመኖር የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ምክር ሊሰጠውና በጸሎት ሊያግዘው ይችላል።

እንዲሁም እግዚአብሔር አጥቢያ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድግባት ስፍራ እንድትሆን ወስኖአል። በርካታ ክርስቲያኖች አጥቢያ ቤተክርስቲያንን የሚመለከቷት እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ነው። በመሆኑም አንድን አዲስ ክርስቲያን ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጋር አንድ እንዲሆን መርዳት፥ አንድን አዲስ ሕፃን ከቤተሰቡ ጋር አንድ እንዲሆን ከመርዳት ጋር ሊነጻጸር ይችላል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፥ እግዚአብሔር ከእርሱ የተሾሙ መሪዎችን ለምሳሌ ሠጋቢዎችን፥ ዲያቆናትንና አስተማሪዎችን በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዲኖሩ ያደረገው ክርስቲያኖች





በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድጉና እንዲበስሉ ለማድረግ ነው (ኤፌ. 4፥11–16)። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉ አገልግሎቶች ለምሳሌ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፥ በኅብረት ማምለክ፥ መመስከር፥ ፍሬያማ አገልግሎትና ትምህርት መስጠት፥ ኅብረትና ዲሲፕሊን ሁሉ አንድ ዐቢይ ዓላማ አላቸው፤ ያም ዓላማ መንፈሳዊ ሕይወትን መመገብና መንፈሳዊ ዕድገትን ማምጣት ነው።

(8). «እውነት» የሆነውን ዐረፍተ ነገር አክብብ።

ሀ. የአንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድገው፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር ኅብረት ቢያደርግና መንፈሳዊ ውሳኔን የሚጠይቁ ከባድ ነገሮች ሲገጥሙት ሌሎች ሰዎች ትክክለኛው የህይወት አቅጣጫ የቱ እንደሆነና እንዳልሆነ እንዲወስኑለት ሲያደርግ ነው።
ለ. የአንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድገው፥ እንደ መንፈሳዊ አባት ሆነው ከሚንከባከቡት፥ ከሚያፈቅሩትና ከሚረዱት የበሰሉ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ሲያደርግ ነው።
ሐ. ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድግበት ስፍራ ናት፤ ምክንያቱም በዚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አለ፤ በኅብረት ማምለክ አለ፤ አገልግሎት መስጠትና ዲሲፕሊን ማድረግ አለ።
መ. በቤተክርስቲያን ውስጥ ኅብረት ስላለ መንፈሳዊ ዕድገትም አለ፤ አንድ ሰው የቤተክርስቲያን አባል ቢሆን፥ ወዲያውኑ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያድጋል፤ ይበስላል።

## ያገኙትን ነገር በሥራ ላይ በማዋል መመገብ

*ዓላማ 8 መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያመጡና የማያመጡ ነገሮች ምን እንደሆኑ ለይ።*

ጤናማና ለሥራ ብቁ የሆነ ሰውነት የተሰጠኝ ለምንድን ነው? ብለን ተገርመን ይሆናል። ጤናማ የሆነ ሰውነት አገልግሎቱ ምንድን ነው? የተሰጠንን ጤናማና ለሥራ ብቁ የሆነ ሰውነት በሚገባ መጠቀም አለብን? ወይስ ዝም ብሎ መቀመጥ አለበት? ጤናማ ሰውነት የተሰጠን ለራሳችን ጥቅም ብቻ ነው? ወይስ ለሌሎችም ኀላፊነት አለብን? ሰውነታችን ሥራ ካልሠራ የተሰጠውን ጤንነትና ብቃት በየጊዜው እያጣ ይሄዳል? ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ስናስብ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ወደ ኅሊናችን ይመጣሉ።

ቀደም ቢል እንደተመለከትነው፥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ፍሬ እንዲያፈሩ መክሮአቸዋል። በዚህ በኢየሱስ ምክር ውስጥ የምናገኘው መንፈሳዊ ጤንነትን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሕይወትን ጭምር ነው (ዮሐ. 15፥1–8)። ከኢየሱስ ንግግር እንደምንረዳው፥ አንድ ሰው ፍሬ ማፍራት አለበት፤ አለበለዚያ መንፈሳዊ ጥፋት ይደርስበታል። የዕድገትም ሆነ የብስለት ግቡ ማገልገልና ፍሬ ማፍራት ነው ክርስቲያኖች በነገር ሁሉ እንዲያድጉ ማሳሰቢያ እንደተሰጣቸው

# 2 ወደ ብስለት ማምራት

## ትምህርት

ግርማና ፀሐይ ወደ ቤተሰባቸው የተቀላቀለውን አዲስ ሕፃን እንዴት መያዝ እንዳለባቸው እየተላመዱ መጥተዋል። ወዳጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ሕፃኑን ዳንኤልን ስመጠየቅ በመምጣታቸው ተደስተዋል። አንዳንዶች «አባቱን ይመስላል» እያሉ ግርማን ያስደስቱታል። ፀሐይም ብትሆን አባትና ልጅ እንደሚመሳሰሉ ተረድታለች። ግርማና ፀሐይ፥ ግርማ ሕፃን ሆኖ የተነሣውን ፎተግራፍ ከአማኑኤል ፎተግራፍ ጋር እያስተያዩ ይደሰታሉ። ሁለቱም በጣም ይመሳሰላሉ።

አንተም እንዲህ ያለ ነገር ገጥሞህ ይሆናል። አንድ ሰው ከቤተሰቦችህ መካከል አንዱን እንደምትመስል ነግሮህ ይሆናል። የቤተሰቦቻችንን ፎቶግራፍ መመልከትና በመካከላቸውም ያለውን መመሳሰል መመልከት እጅግ የሚያስደስት ነገር ነው።

ልክ እንዲሁ በክርስቲያናዊ ሕይወትም ውስጥ አንዳንድ «ተመሳሳይና ተዛማጅ» ነገሮችን እናገኛለን። ኢየሱስ የራሱን ሕይወት ሰጥቶናል። አማኞች በነገር ሁሉ እየበሰሉ ሲሄዱ የኢየሱስ ሕይወት ይበልጥ ይገለጥላቸዋል። በዚህ ክፍል የመንፈሳዊ ዕድገት ግብ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ እንማራለን። ከዚህ በተጨማሪ በዕድገትና በብስለት ሂደት ውስጥ ምን ምን ነገሮች እንደሚካተቱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ነገር እንመለከታለን። በዚህ ክፍል የምንማረው ነገር ሌሎች በነገር ሁሉ እንዲበስሉ ለምንሰጠው አገልግሎት ትልቅ ትምህርት እንደሚሰጠን እናረጋግጣለን።

### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ክርስቶስን መምሰል
- ሰዎችን ሙሉ ማድረግ (ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ሙላት ማድረስ)
- ደረጃ በደረጃ





### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

- ይህን ትምህርት ስትጨርስ፦
- የመንፈሳዊ ዕድገት ግብ ምን እንደሆነ በትክክል መግለጽ ትችላለህ።
- ሰዎችን ወደ ክርስተስ ሙላት ለማድረስ የምገባ ሚና ምን እንደሆነ መለየት ትችላለህ።
- አንድ ሰው ከሕፃንነት ወደ መንፈሳዊ ብስለት የሚያልፍበትን ሂደት መናገር ትችላለህ።

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

## ክርስቶስን መምሰል

### *መንፈሳዊ ዕድገት ከእያንዳንዱ ይጠበቃል*

*ዓላማ 1 ክርስቲያኖች ክርስቶስን መምሰል ያለባቸው ለምን እንደሆነ የሚገልጹትን ዐረፍተ ነገሮች ለይ።*

ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ የየራሱ የሆነ የተለየ ባሕርይ አለው። ሕይወት የራሱን የተለየ ባሕርይ የሚያገኘው በመራባት ነው። ዘር ሕይወት አለው። ሕይወት ለዕድገት ተስማሚ የሆነውን ነገር ካገኘ ባሕሪውን ይገልጣል። ለምሳሌ ሩዝ፥ በቆሎ፥ ባቄላ ወይም ማንኛውንም ዐይነት ዘር ብንተክል ከጥቂት ጊዜ በኋላ የምናገኘው ምን እንደሆነ እናውቃለን። ለሕይወት የራሱን የተለየ ባሕርይ የሚሰጠው ነገር የሚገኘው በዘሩ ውስጥ ነው። ዘሩ ተስማሚ የሆነ ነገር ሲያገኝ በዘሩ ውስጥ ያለው ሕይወት ይገለጣል፤ እያደገም ይሄዳል።

ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ስንነጋገር ይህን እውነት ማጤን በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት የሚሰጠን «አዲስ ሕይወት» የራሱን ሕይወት ነው። እግዚአብሔር የሚሰጠን ሕይወት የራሱ የሆነ የተለየ ባሕርይ አለው። ይህ «አዲስ ሕይወት» ተስማሚ መንፈሳዊ ምግብ ሲያገኝ እያደገና እየበሰለ ይሄዳል፤ እኛም በየጊዜው እርሱን እንመስላለን። የእኛ ኀላፊነት መንፈስ ቅዱስ የሚለንን ነገር መስማትና አዲሱን ሕይወታችንን እንደፈቃዱ እንዲቀርጽና እንዲቆጣጠር መፍቀድ ነው (ሮሜ 8፥5–11፤ ገላ. 5፥25)።

(1). «እውነት» የሆነውን ዐረፍተ ነገር አክብብ

ሀ. የክርስቲያኖች ሕይወት ባግባቡ ከተመገበ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያድጋል።
ለ. አንድ ሰው አዲስ ሕይወትን በተቀበለ ጊዜ መንፈሳዊ ሕይወቱ ወዲያውኑ ያድጋል።
ሐ. በመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ውስጥ ትልቁ ኀላፊነታችን ለመንፈስ

ምክር ይጠቅማል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች አንድ ግብ እንዳላቸው ልብ እንበል፤ ግቡም የእግዚአብሔርን ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ማዘጋጀት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን ነገር እንድንሆን ያዘጋጁናል፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ሰውን ሙሉ ለማድረግ ይጠቅማሉ ማለት እንችላለን። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ ከፈለግን፥ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት አለብን፤ ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት የምንፈልግ ከሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያጠና ልንረዳው ያስፈልጋል።

(12). «እውነት» የሆኑትን ዐረፍተ ነገሮች አክብብ።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ሙሉ ሆነው እንዲያድጉ ዐይነተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፤ ምክንያቱም ለመንፈሳዊ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ መርሆችን ይሰጠናል።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ዕድገት ወሰንና ድንበር እንዳለው ይናገራል።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጥልናል፤ ለመንፈሳዊ ዕድገት መሠረታዊ የሆኑና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለማድረስ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ይሰጠናል።

መ. መጽሐፍ ቅዱስ ልንከተለው የሚገባንን እውነተኛ ምሳሌ በኢየሱስ ክርስቶስ አሳይቶናል።

ሠ. መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናው ዕውቀታችንን ለማስፋትና መንፈሳዊ ሰዎች መሆናችንን ለሌሎች ለማሳየት ነው።

በዚህ ትምህርት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ የተማርነውን ነገር ባጭሩ እንከልስ። የበሰሉ ክርስቲያኖች ክርስቶስን እንደሚመስሉ ተገንዝበሃል። በክርስቶስ አዲስ ሕይወት የተቀበሉ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ በዚህ ዐይነት የክርስቶስ ሕይወት በእነርሱ ውስጥ የበለጠ ይገለጣል። በክርስትና ሕይወት ለመብሰል፥ ሕይወታችንን በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት እንዳለበት ተምረሃል። በክርስቲያናዊ ምግባ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ትልቁ አገልግሎት ሰዎች ክርስቶስን እንዲመስሉ መርዳት እንደሆነ ተገንዝበሃል። ሰዎች በሕይወታቸው ሙሉ እንዲሆኑ ለማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ተምረሃል። እነዚህን መሠረታዊ ሐሳቦች በሚገባ ካልተረዳህ፥ ወደሚቀጥለው ክፍል ከማለፍህ በፊት በዚህ ትምህርት ውስጥ ያጠናኸውን ነገር እንደገና ከልስ።

## ደረጃ በደረጃ

### የክርስቲያናዊ ምግባ ግብ

*ዓላማ 9 በክርስቲያናዊ ምግባ ውስጥ በመካከለኛና በመጨረሻ ግብ መካ ከል ያለውን ልዩነት ለይ።*

አንድ ሕፃን ሲወለድ፥ ማደግ ይጀምራል። ሕፃኑ ጎልማሳ እስኪሆን ድረስ ያድጋል፤ በየጊዜው እየበሰለ ይሄዳል። ከሕፃንነት እስከ ጉልምስና ያለው የዕድገት ሂደት፥ ጊዜ እንደሚወስድ እናውቃለን። ቀደም ሲል የዕድገትና የብስለት ደረጃዎች እንዳሉ ተምረናል። በእያንዳንዱ የዕድገት ደረጃ ውስጥ





ሕፃኑ እያደገ መሆኑን የሚያሳዩ ነገሮች እንዳሉ እናስተውላለን፤ ለምሳሌ ሕፃኑ ቀስ በቀስ መናገር ይጀምራል። በእያንዳንዱ የዕድገት ደረጃ ውስጥ የሚታዩት ለውጦች «መካከለኛ ግብ ይባላሉ። እነዚህ መካከለኛ ግቦች ወደ ጉልምስና ደረጃ የሚያደርሱ በመሆናቸው መሰስተኛ ዓላማን ይወክላሉ። እነዚህ መካከለኛ ዓላማዎች በራሳቸው መልካም ናቸው፤ ሆኖም እነዚህ መካከለኛ ዓላማዎች ወደ «መጨረሻው ግብ» የሚደርሱ ደረጃዎች እንደሆኑ ስንገነዘብ የበለጠ መልካም መሆናቸውን እናስተውላለን። እነዚህን አሳቤዎች መረዳት ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዴት ማሟላት እንደምንችል የበለጠ ያስተምሩናል።

መንፈሳዊ ሕይወት በዕድገቱ ከተፈጥሮአዊ ሕይወት ጋር ተመሳሳይ ነው። አንድ ሰው አዲስ ሕይወት ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ ይጀምራል። የአማኞች መንፈሳዊ ሕይወት የመጨረሻው ግብ ክርስቶስን መምሰል ነው (ሮሜ 8፥29፤ 12፥2፤ 2ቆሮ. 3፥18)። አንድ ሰው መንፈሳዊ ጉዞውን ሲጀምር፥ በትክክል ለማደግ የሚያስፈልጉትን ነገሮች መመገብ አለበት። የቃሉን ወተት ለመመገብ መመኘት አለበት (1ጴጥ. 2፥2)። ከዚያም በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ መመዘኛዎችን ይማራሉ። በዕድገቱ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ምን ማድረግ እንዳለበትና በሕይወቱ የሚጠበቀው ነገር ምን እንደሆነ እየተረዳ ይመጣል። ባጭር አነጋገር «መራመድን ይማራል»። የእግዚአብሔርን ቃል እየተጠማና የተማረውንም ነገር በሕይወቱ እየተለማመደ ሲመጣ እምነቱ ያድጋል። የእግዚአብሔርን ቃል እየተረዳ ሲሄድ የመንፈሳዊ ውጊያን ባሕርይ እየተማረና (ኤፌ. 6፥10–18) የነፍሱን ጠላት እየለየ ይመጣል። ከበሰሉ ክርስቲያኖች ጋር ይበልጥ እየተቀራረበ ሲሄድ፥ መንፈሳዊ ድል የሚገኘው በጸሎት መሆኑን ይረዳል። ወደፊት እየገሰገሰና በቃሉ እየበረታ ሲሄድ እንዲሁም ከጌታና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለው ኅብረት እየጠነከረ ሲሄድ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገና እየበሰለ ይሄዳል። ወደ መጨረሻው ግብ እየገሰገሰ ሲሄድ በየጊዜው ክርስቶስን እየመሰለ ይሄዳል። ቃሉን ዘወትር ለመመገብ መመኘት፥ በጸሎት መትጋት፥ እውነትን ከሐሰት ለመለየት መማር በአንድ ጊዜ የምንማራቸው ነገሮች አይደሉም። እነዚህ እያንዳንዳቸው የመካከለኛ ግብ ደረጃ ቢሆኑም ክርስቶስን ለመምሰል ግን የመጨረሻ ግቦች ናቸው።

የክርስቲያናዊ ምግባ የመጨረሻው ግብ፥ አንድ ሰው በነገር ሁሉ እንዲያድግና ክርስቶስን እንዲመስል መርዳት ነው።

(13). በሚቀጥሉት ሐሳቦች ውስጥ በክርስቲያን ምግባ ውስጥ የመካከለኛ ውን ግብ ለሚያመለክተው ቁጥር "1" ጻፍ። እንዲሁም በክርስቲያ ናዊ ምግባ ውስጥ የመጨረሻውን ግብ ከሚያመለክተው ፊት ለፊት ቁጥር "2"ትን ጻፍ።

_____ሀ. አዲስ አማኝን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያነብና ሕይወቱን በዚህ መሠረት ላይ እንዲያደርግ ማስተማር።

_____ለ. አማኞችን ቀስ በቀስ የሕይወታቸውን አቅጣጫ ወደ ክርስቶስ መምሰል የሚለውጠውን የመንፈሳዊ ዕድገትን መመሪያዎች ማስተማር።

እግዚአብሔር የሰጠህን ስጦታ መጠቀም ስትጀምር፥ የሰዎች ሕይወት በአስደናቂ ሁኔታ ሲለወጥ ታያለህ፤ ደግሞም እንዲያድጉ የምትረዳቸው ሰዎችም ሆኑ አንተ ራስህ ስታድግ ታያለህ። መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድግ መመገብ እንዲህ ያለ በረከት ያስገኛል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መለኮታዊ ስልት
- መለኮታዊ ስጦታዎች
- የመንፈሳዊ ዕድገት የምገባ መንገድ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት እጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ

- ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ከመንፈሳዊ ዕድገት ጋር ያለው ዝምድና ምን እንደሆነ የሚገልጹትን ሐሳቦች ትረዳለህ፤
- የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ፥ ለአገልግሎት የሚሰጡን ስጦታዎችና የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከመንፈሳዊ ዕድገት ጋር ያላቸው ዝምድና ምን እንደሆነ መግለጽ ትችላለህ፤
- መንፈሳዊ ዕድገትን ለማምጣት መደበኛና መደበኛ ያልሆኑት መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት ትችላለህ።

---

የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

## መለኮታዊ ስልት

ክርስቲያኖች ሕያው ናቸው፤ በመሆኑም በየጊዜው ያድጋሉ፥ ክርስቶስንም እየመሰሉ ይሄዳሉ። እንግዲህ የቤተክርስቲያንና የበሰሉ ክርስቲያኖች ተልዕኮ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው። መንፈሳዊ ዕድገትን እንዴት ማምጣት ይቻላል ብለህ ትገረም ይሆናል። ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ እንደሚያድግና እኛም ሕይወት ካለው ነገር ዕድገትን እንደምንጠብቅ ተምረሃል፤ ይሁን እንጂ ትክክለኛ ዕድገት የሚኖረው ለዕድገት የሚያስፈልጉት ነገሮች ሲሟሉ ነው። ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት በሚለው ርዕስ ስር ትክክለኛ ዕድገት ሊኖር የሚችለው ምን ምን ነገሮች ሲሟሉ እንደሆነ እንማራለን። መጽሐፍ ቅዱስ ደቀ መዛሙርት ማድረግ የሚል መለኮታዊ ስልት እንዳለ ያስተምረናል።

ደቀ መዝሙር ምንድን ነው?

*ዓላማ 1 ደቀ መዝሙር ምን እንደሆነና የክርስቲያናዊ ምገባ ግብ ምን እንደሆነ የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*





አንዳንድ ጊዜ ደቀ መዝሙር የሌሎችን ሰዎች ትምህርት የሚከተል «ተከታይ» ተደርጎ ይታያል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደቀ መዝሙር ማለት «ተማሪ» ማለት ነው። ሆኖም ደቀ መዝሙር «ተማሪ» ነው ሲባል ጥልቅ ትርጉም አለው። ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል ከሌላ ሰው ጋር ኅብረትና አንድነት ማድረግን ያካትታል። ስለዚህ አንድ ሰው ደቀ መዝሙር ነው ሲባል ከመምህሩ ጋር ኅብረትና አንድነት አለው ማለት ነው። አንድ ተማሪ የመምህሩን ውስጣዊ አመለካከት ላያገኝ የመምህሩን ትምህርት ብቻ ሊያገኝ ይችላል። አንድ ደቀ መዝሙር ከመምህሩ ይማራል፤ ደግሞም የመምህሩን ውስጣዊ አመለካከት፥ ተግባርና ለነገሮች ያለውን አስተያየት ይካፈላል። ደቀ መዝሙር መምህሩን ይመስላል። ለመምህሩ ታማኝ ነው፤ መምህሩንም ለመምሰል ይመኛል። ደቀ መዝሙር መምህሩን ለመምሰል ይጥራል፤ መምህሩ የሚያደርገውን ነገር እርሱም ለማድረግ ይሞክራል፤ ስለዚህ አንድ ሰው ደቀ መዝሙር ነው የሚባለው መምህሩ በቃልም ሆነ በድርጊት የሚያስተምረውን ነገር በሙሉ ልቡ ለመቀበል ዝግጁ ሲሆን ነው። የአንድ ደቀ መዝሙርና የአንድ መምህር ግንኙነት ሁለት ሰዎችን የሚያካትት በመሆኑ «መደበኛ ያልሆነ ግንኙነት» ይባላል፤ እንዲህ የተባለበትም ምክንያት አንደኛው ሰው (መምህሩ) ያስተምራል፥ ያለውን ዕውቀት ያካፍላል፤ ሌላኛው ሰው (ደቀ መዝሙሩ) ያየውን ነገር ለመውረስ ይሞክራል። ይህ ዐይነቱ ግንኙነት በአንድ ተማሪና በአንድ የትምህርት ቤት መምህር መካከል ካለው «መደበኛ ከሆነ ግንኙነት» የተለየ ነው።

ደቀ መዝሙር ምን እንደሆነ ለመረዳት የንግድ ሥርዐትን ለመማር ከአንድ አዋቂ ዘንድ የሄደን ሰው መመልከት ይጠቅመናል። ራሱ መምህሩ አሁን የተካነበትን የንግድ ሥርዐት የተማረው ከሌላ ሰው ነው። ይህ ሰው አሁን ያገኘውን ዕውቀት እስኪቀስም ድረስ እያንዳንዱን እርምጃ እየተከታተለ ከሚያስተምረው መምህር ስር ሆኖ በቂ ትምህርት ወስዷል። ሰውየው በንግድ ሥራው ላይ ሳለ ችግር ሲገጥመው ወደ መምህሩ ዘንድ ይመጣና ከመምህሩ ጋር ጥቂት ጊዜ ያሳልፋል። በዚህ ጊዜ መምህሩ ሥራውን እንዴት እንደሚሠራ ከመምህሩ ጎን ሆኖ ይመለከታል፤ ከዚያም ከመምህሩ የተማረውን ነገር እርሱም በሥራ ላይ ያውላል። መምህሩን ለመምሰል ይጥራል፤ ሰውየው መምህሩን ለመምሰል በሚያደርገው ጥረት ውስጥ የራሱን ዘዴና ችሎታ ያዳብራል። በዚህ ዐይነት የንግድን ሥርዐት ለመማር ወደ አንድ መምህር ዘንድ የሄደው ሰው መምህሩን መስሎ ይመለላል። መምህሩ የሰጠውን ትምህርት ሁሉ በሥራ ላይ በማዋል መምህሩን እየመሰለ ይሄዳል። እንግዲህ የንግድን ሥርዐት ለመማር የሄደው ሰው ከመምህሩ የሚማረው መምህሩን በመከተልና በመምሰል ነው።

ደቀ መዛሙርት ማድረግ በአንዳንድ ነገር የንግድን ሥርዐት ለመማር የሄደው ሰው ያደረገውን ነገር ይመስላል። በመካከላቸው ካለው ግንኙነት የተነሣ የንግድን ሥርዐት ለመማር የሄደው ሰው በብዙ ነገር መምህሩን እንደሚመስል መገመት እንችላለን። የንግድን ሥርዐት ለመማር የሄደው ሰው ከመምህሩ ጋር አብሮ በመሆንና መምህሩንም በመምሰል የመምህሩን ችሎታ፥ ዕውቀትና ዘዴ ተምሮአል። ልክ እንዲሁ አንድ ደቀመዝሙር መምህሩን ይመስላል።

በእሳት የተቃጠሉ ወይም ከፉኛ የተጎዱ ሰዎች አይተህ ይሆናል። ቁስሉ ተገቢ ሕክምና ካላገኘ ቶሎ ይመረቅዛል። ቁስሉ ከመረቀዘ ደግሞ በሽተኛው የበለጠ ይታመማል። በዚህ ጊዜ አካሉ የቆሰለውን ክፍል ለመርዳት ይረባረባል፤ በዚህ ዐይነት አካሉ እየዳነ ይሄዳል። የተጎዳው የአካል ክፍል እንዲፈወስ የአካሉ ሁሉ ምኞት ነው። ስለዚህ አንድ የአካል ክፍል ሲጎዳ መላው የአካል ክፍል የተጎዳውን ክፍል ለመርዳት ስለሚረባረብ የተጎዳው የአካል ክፍል ብቻ ሳይሆን መላው አካል ይደከማል፤ ዕረፍትም ይፈልጋል። ምክንያቱም መላው አካል የተጎዳውን ክፍል ለመታደግ ያለውን ኀይል ሁሉ ጨርሷል።

በክርስቶስ አካል ማለትም በቤተክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱ የአካል ክፍል ወይም አባል የደከሙና ያላደጉ የአካል ክፍሎች ጤናማና ሙሉ እንዲሆኑ የበኩላቸው ተግባር ይፈጽማሉ። ደካማና ያልበሰሉ አባላት ብርቱና ሙሉ ከሆኑ አባላት የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ ያገኛሉ።

ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ቤተክርስቲያን ዐይነተኛ አገልግሎት ትሰጣለች፤ ምክንያቱም አንዱ አባል ለሌላው አባል እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ቤተክርስቲያን ሰዎችን በሚወዱ፥ በሚንከባከቡና ለሰዎች ርኅራኄን በሚያሳዩ ሰዎች የተገነባች ሕያው አካል በመሆኗ፥ ለመንፈሳዊ ዕድገት ትልቅ መሠረት ናት። እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቲያናዊ ምገባ የቤተክርስቲያን አገልግሎት (ተግባር) ነው፤ ቤተክርስቲያን ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምትረዳቸው በአካሉ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ፥ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ትርጉም ያለው ኅብረት ማድረግ እንዲችሉና በክርስቶስ አካል ውስጥ የተሰጣቸውን ተግባር ከግቡ እንዲያደርሱ ነው።

(10). ከ1-3 የተቀመጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ስለ ቤተክርስ ቲያን ወይም ስለ አካል ከተሰጡት ኃሳቦች ጋር አዛምዳቸው።

1. ሮሜ 12:1-8 2. 1ቆሮ. 12:12-27 3. ኤፌ. 4:11-16

ሀ. የአንድ ሰው ሥጦታ የሚወሰነው ባሰው የእምነት መጠንና በአካሉ ፍላጎት ነው።

____ለ. ሥጦታዎች ወይም አገልግሎቶች በክርስቶስ አካል ውስጥ የተሰጡት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት፣ ለመንፈስ አንድነት፣ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ለማሳወቅና ለመንፈሳዊ ሕያወት ብስለት ነው።

____ሐ. የክርስቶስ አካል የተገነባው አንዱ በሌላው ላይ የሚደጋገፍና እያንዳንዱ ክፍል አካሉ እንዲሰራ ጠቃሚ ክፍል ሆኖ ነው።

____መ. ለሰው የተሰጡትን የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎች ሲለማመ ዳቸው በትህትና እንዲያመሰግን እንጂ ስለተሰጡት ስጦታዎች እንዲታበይ አይደለም።

____ሠ. የክርስቶስ አካል እርስ በርሱ የሚተሳሰብ ክፍል ስለሆነ አንዱን ክፍል የሚነካ ጉዳይ አካሉን ሁሉ ይነካል።

____ረ. የአካሉ አገልግሎቶች በመንፈሳዊነት ሙሉ ሰው መሆንን፣ የአካሉን ፍላጎትና ያሀም ፍላጎት የሚሟላበትን መንገድ ማወቅን ያስገኛሉ።





____ሰ. እግዚአብሔር የተለያዩ አገልግሎቶችን ለአካሉ ሰጥቷል።

(11). እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ቤተ ክርስቲያን እርስ በርሳቸው ከሚደጋገፉ የተለያዩ ክፍሎች የተሠራች ህያው አካል ነች።
ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱ አባል ሙሉ እንዲሆንና ከሌላው ተነጥሎ ለብቻው እንዲንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።
ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደካማና ያልበሰሉ አባላት ከጠንካሮችና ከበሰሉ አባላት መረዳትንና እንክብካቤን ያገኛሉ።
መ. የክርስቶስ አካል አንዱ ክፍል በሚገባ ባያድግ መላው አካል ይጎዳል።
ሠ. የክርስቲያናዊ ምገባ ግብ ግለሰብን ለመገንባት ሲሆን፥ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት አይመለከትም።

## የአገልግሎት ሥጦታዎች

*ዓላማ 7 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለመንፈሳዊ ዕድገት እንዴት ጥቅም እንደሚሰጡና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የተቀበለ ሰው ኀላፊነት ምን እንደሆነ የሚገልጹትን ዐረፍተ ነገሮች ለይ።*

እያንዳንዱ አማኝ በክርስቶስ አካል ውስጥ የተሰጠውን አገልግሎት እንዲያከናውን ከእግዚአብሔር ስጦታን (ወይም ስጦታዎችን) ተቀብሎአል። ክርስቲያኖች ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንደተቀበሉ አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያስተምራሉ፦

ሮሜ 12:1-8፣ 1ቆሮ. 12፣ ኤፌ. 4:11-16 እና 1ጴጥ. 4:10-11 ናቸው።

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ አጥና። እነዚህ ክፍሎች ስለ መንፈሳዊ አገልግሎት ትልቅ ትምህርት ይዘዋል። ከዚህ የሚከተሉት ነጥቦች ክፍሎቹ የሚያስተምሩትን እውነት በአጭሩ ይናገራሉ፦

1. እያንዳንዱ አማኝ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ተቀብሎአል።
2. እነዚህ ስጦታዎች የተሰጡት በመንፈስ ቅዱስ ነው።
3. በአካሉ ውስጥ ያሉት የአካሉ ክፍሎች አንድ ዐይነት ስጦታ አልተቀበሉም፤ ወይም ሁሉም አንድ ዐይነት አገልግሎት አያገለግሉም።
4. አካሉ የሁሉንም ስጦታዎች አገልግሎት ይሻል።
5. ስጦታዎቹ የተሰጡት ለፍሬያማ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ነው።
6. ስጦታዎቹን በተገቢው መንገድ መጠቀም ለአካሉ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ ነው።

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሰዎችን ደቀ መዝሙር የማድረግ አገልግሎትን የሚያዩት በተለየ መልክ ነው። ሰዎችን ደቀ መዛሙርት የምናደርገው በቤተክርስቲያኒቷ ውስጥ ባሉት መደበኛ አገልግሎቶችና ከሰዎቹ ጋር ግንኙነት በማድረግ ነው የሚል አመለካከት አላቸው። ስክርስቲያናዊ ምገባ ያለን አመለካከት የተለያየ ቢሆንም ክርስቲያናዊ ምገባ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ስልቶች ያስፈልጉታል።

የትኛውንም ዐይነት መንገድ ብንከተል፥ መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያመጣው መንፈሳዊ ምግብ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ደቀ መዝሙር ከምናደርጋቸው ሰዎች ጋር የሚኖረን የቅርብ ግንኙነት፥ ለመንፈሳዊ ዕድገት የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አለው። የእግዚአብሔርን እውነት የምናስተላልፍበት መንገድ ብዙ ጊዜ ሲሠራበት የነበረ መደበኛ መንገድ ነው፤ አስተማሪው ያስተምራል፥ ተማሪው ይማራል። የቅርብ ግንኙነት በማድረግ ስናስተምር አሁን መደበኛ ባልሆነ መንገድ እያስተማርን ነው፤ የበሰሉ ክርስቲያኖች ካልበሰሉ ክርስቲያኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት እያደረጉና ምሳሌ እየሆኑ ክርስቲያናዊ ሕይወትን እንዴት መኖር እንዳለባቸው በተግባር ያሳዩአቸዋል። ያልበሰሉ ክርስቲያኖች ከበሰሉ ክርስቲያኖች ጋር ጊዜ በመውሰድና እነርሱን በመምሰል ይማራሉ። እንግዲህ መንፈሳዊ ሕይወትን የማሳደግና የመመገብ አገልግሎት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሊከናወን ይችላል ማለት ነው።

ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋር የነበረው ግንኙነት በክፍል ውስጥ አንድ አስተማሪ ከተማሪዎቹ ጋር ካለው ግንኙነት በጣም የተለየ ነው። ኢየሱስ የመረጣቸውን ሰዎች ደቀ መዛሙርት ለማድረግ የተጠቀመበት መንገድ ክርስቲያናዊ ምገባን መደበኛ ባልሆነ መንገድ እንዴት እንደምናከናውን ትልቅ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል።

በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚታየው ግንኙነትና የአካሉ ክፍሎች በተሰጣቸው ስጦታ አንዱ ሌላውን ለማገልገልና ለማሳደግ የሚያሳዩት ትብብር፥ ቤተ ክርስቲያን ከአካሉ ክፍሎች ወይም ከአባሎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በሚያደርጉ አስተማሪዎች የምትታነጽ መሆኗን በግልጽ ያመለክተናል። በዚህ መንገድ የሚመጣው ዕድገት መደበኛ ያልሆነ ክርስቲያናዊ ምገባ ይባላል።

መደበኛ በሆነ መንገድ የምናከናውነው ክርስቲያናዊ ምገባ በአብዛኛው የሚያተኩረው እውነትንና ዕውቀትን በማስተላለፍ ላይ ነው። መደበኛ በሆነ መንገድ በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን፥ የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮና መንፈሳዊ ዕውቀቶችን ማስተማር ይቻላል። ይህ መደበኛ የማስተማሪያ መንገድ በትምህርት ቤት ውስጥ አስተማሪዎች ከሚጠቀሙበት ስልት ጋር ተመሳሳይ ነው። ኢየሱስ በዎችን ደቀ መዛሙርት በሚያደርግበት ወቅት ብዙ ጊዜ የሚሠራበትንና መደበኛ የሆነውን የማስተማሪያ ስልት ተጠቅሞአል። እርግጥ ነው በሚያስተምርበት ወቅት የማስተማሪያ ክፍሎችን አልተጠቀመም፤ ሆኖም መደበኛ የሆነውን የማስተማሪያ ስልት በሚገባ ተጠቅሞበታል። የክርስቲያናዊ ምገባ ዓላማ የሰዎችን ጭንቅላት በዕውቀት መሙላት ሳይሆን ክርስቶስን ማእከል ያደረገ ሕይወት እንዲኖሩ መርዳት ነው፤ እርግጥ ክርስቶስን ማእከል ያደረገ ሕይወት ለመኖር ዕውቀት ያስፈልጋል። ሳልበሰሉ





ክርስቲያኖች ዕውቀትን ለማስተላለፍ ክፍሎች፥ ዐውደ ጥናቶችና ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ጥሩ መንገዶች ናቸው። ይህ ዕውቀት ሕይወትን የሚለውጥ ዕውቀት በመሆን ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲበስሉና ክርስቶስንም የበለጠ እንዲመስሉ ያግዛቸዋል።

ፍሬያማ ክርስቲያናዊ ምገባ መደበኛውንና መደበኛ ያልሆነውን የማስተማሪያ ስልት ያካተተ ነው። ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምንረዳቸው ከሆነ ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠር አለብን። የክርስቶስን ሕይወት ልናሳያቸውና ክርስቶስን እየመሰሉ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ምሳሌ ልንሆናቸው የምንችለው አብረናቸው ስንኖር ነው። ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱሳዊና አስተምህሮአዊ እውነቶችን እንዲረዱ የምንፈልግ ከሆነ መደበኛውን የማስተማሪያ ስልት ተከትለን ማስተማር አለብን። ክርስቲያናዊ ምገባ ሁለቱንም ማለትም መደበኛና መደበኛ ያልሆነውን የማስተማሪያ ስልት ያካትታል። ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምንረዳቸው ከሆነ ሁለቱንም የማስተማሪያ ስልቶች መጠቀም አለብን።

(17). መንፈሳዊ ዕድገት እንዲመጣ በሚደረገው ክርስቲያናዊ ምገባ ውስጥ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ አካሄዶችን ለይ። ለመደበኛ አካሄድ ምሳሌ የሆኑትን "1" ቁጥርን፣ መደበኛ ሳልሆኑት የቀረቡትን ምሳሌዎች ደግሞ "2" ቁጥር በመስጠት ለይ።

ሀ. ኢየሱስ መንፈሳዊ ዕድገት እንዲኖር የተከተለው ምገባ ከአሥራ ሁለቱ ጋር አብሮ በመሆን ነው።
ለ. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ስለ ክርስትና ሕይወት ራሱን እንደ ምሳሌ እንዲያቀርብ ይመክረዋል።
ሐ. መጋቢ በሪሁን በክርስትና ሕይወታቸው ለማደግ የሚሹትን ተከ ታታይ ትምህርቶች ያስተምሯቸዋል። ተማሪዎቹ የቤት ሥራቸውን መሥራትና ትምህርቱን በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ይጠበቅባቸዋል።
መ. መጋቢ ደቦጭ ምዕመኑን በቡድን በማደራጀት በየወሩ ስብሰባ እንዲ ያደርጉና ኅብረት እንዲኖራቸው፣ እንደተሰማቸውም እንዲጸልዩና ቃሉን እንዲያጠኑ አድርገዋል።
ሠ. ጳውሎስ በገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ ህግን ጠንቅቆ እንዳጠና ይገልጻል።

# 4 ማወቅና ማድረግ

## ትምህርት

ግርማ ዳቦ እንዴት እንደሚጋገር መመሪያ የሚሰጠውን መጽሐፍ ፀሐይ በማግኘቷ በጣም ደስ አለው። ይህን መጽሐፍ የፀሐይ እናትና አያት ለብዙ ዓመታት ሲጠቀሙበት ነበር። የፀሐይ ቤተሰቦች የሚጋግሩትን ዳቦ በጣም ይወደዋል። ሁልጊዜ ትኩስና ጣፋጭ ዳቦ ነው። ፀሐይ መጽሐፉን ካነበበች በኋላ እቃ ቤት አለቀመጠችው። እርሷና ግርማ ከተጋቡ ጀምሮ እንደምታደርገው ሁሉ አሁንም የዳቦ ሊጡን ድሮ ከምትጠቀምባቸው ቅመሞች ማዘጋጀቷን ቀጠለች። አንድ ዳቦ ጋግራ እንዳወጣች የማሪያ ዳቦ እንደ እናቷ ዳቦ ዐይነት እንዳልሆነ ግርማ አወቀ። ፀሐይ ጣፋጭ ዳቦ እንዴት እንደሚጋገር መመሪያ የሚሰጣትን መጽሐፍ ሳትከተል እንደ ድሮዋ የዳቦ ሊጡን ማዘጋጀት ቀጠለች። መጽሐፉ የሚሰጠውን መመሪያ ካልተከተለች ፀሐይ የምትጋግረው ዳቦ እንደ እናቷ ዳቦ ጣፋጭ ሊሆን አይችልም።

አዲስ ነገር ተምረሀ፣ የተማርኸውን ነገር ወዲያውኑ በሥራ ላይ ሳታውል የቀረህበትን ጊዜ ታስታውስ ይሆናል። መማር እውነትን ማወቅን ያካትታል፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም። መማር ያወቅነውን እውነት በሥራ ላይ ማዋልና በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ መለማመድን ያጠቃልላል። በዚህ ትምህርት ውስጥ፣ መማር እውነትን ማወቅና ያወቅነውን እውነት በሥራ ላይ ማዋልና የባሕርይ ለውጥ ማምጣት እንደሆነ እንማራለን።

### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ሁለቱ የመማር እሳቤዎች
- የተማሪውን አመለካከት መለወጥ
- የመማር ደረጃዎች
- ሰዎች እንዴት ይማራሉ?
- ለለ ክርስቲያናዊ ዕድገት ምገባ መማር





### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት አጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ፦

- የአንድ ሰው ዕውቀት፣ አመለካከትና ባሕርይ እንዲለወጥ ከተፈለገ ሰውየው የተማረውን ነገር በሚገባ ማውጠንጠንና ከሕይወቱ ጋር ማዛመድ አስፈላጊ መሆኑን ትገነዘባለህ።
- ሰዎች አንድን ነገር የሚማሩት በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ውስጥ ሲያልፉና ከቀላል እስከ ከባድ የትምህርት ዐይነቶችን ሲማሩ እንደሆነ ትረዳለህ፤
- በክርስቲያናዊ ምገባ አገልግሎት ላይ የተማሩ ሰዎች፣ ተማሪዎች በአስተሳሰባቸው፣ በአመለካከታቸውና በሕይወ ታቸው ክርስቶስን እየመሰሉ እንዲሄዱ ምን ዐይነት መንፈሳዊ እውነት ማስተማር እንዳለባቸው ትረዳለህ፤

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

## ሁለቱ የመማር እሳቤዎች

*ዓላማ 1 ሰዎች አንድን ነገር የሚማሩት፣ ትምህርቱ ከአስተማሪው ወደ ተማሪው እንዳለ ሲዛወር ነው ወይም ተማሪው ራሱ ትምህርቱን እንዲገነዘብና እንዲያውቅ ሲደረግ ነው የሚለውን ብሂል መርምር።*

ስለ መማርና ማስተማር የራስህ መረዳት እንዳለህ አልጠራጠርም። ሙያዊ ወይም መደበኛ ትርጉም ሳትሰጥ ትችላለህ። ነገር ግን እነዚህን ቃላት ምን ዓ ይነት ኃሳብ እንዳዘሉ የራስህ ግንዛቤ አለህ።

(1). ለእነዚህ ቃላት በተረዳኸው መጠን ቀለል ያለ ትርጉም ስጣቸው።
ሀ. መማር ማለት. . .
ለ. ማስተማር ማለት. . .

እነዚህን ቃላት በተረዳኸው መጠን እንድትጽፍ ተጠይቀሃል። የምታ ስበውን ስለጻፍክ ትክክለኛ የሆነ ወይም ያልሆነ መልስ የለም። ብዙ ሰዎች ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከታወቁት ሁለት አመለካከቶች አንዱን ወይም ሌላውን ይደግፋሉ። እነዚህን አመለካከቶች በማብራራበት ጊዜ የአንተ ኃሳብ ከየትኛው ጋር እንደሚስማማ ማየት ትችላለህ።

አንዳንድ ሰዎች አንድን ነገር መናገር እንደ ማስተማር፣ መስማትን ደግሞ እንደ መማር ይቆጥሩታል። አንድ ሰው ታሪክ ቢናገር፣ እውነትን ቢተነትን ወይም መረጃን ቢያብራራ እንዳስተማረ ይቆጠራል። እንዲሁም አንድ ሰው አስተማሪው እነዚህን ነገሮች ሲያስተምር ቢሰማ እንደተማረ ይቆጠራል። ተማሪው አስተማሪው የሚናገረውን ነገር እንዲጽፍ ወይም በቃሉ እንዲያጠና ይደረግ ይሆናል። ተማሪው ከጊዜ በኋላ አስተማሪው የተናገረውን ነገር ሁሉ

(3). ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ክፍሎች ብዙ የመማር ሂደት የሚካሄድ በት የትኛው ይመስልሃል? በቀደመው እውቀትና ልምድ ላይ ለመገንባትና ተማሪው ለችግሮች መፍትሔ እንዲፈልግ የሚያደርገው የትኛው ነው? ለምን? መልስህን በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፈው።

ብስራት በአብዛኛው የገዘወራ ትምህርትን አመለካከት የምትከተል ትመበላለች። በምታስተምርበትና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በምትናገርበት ጊዜ ህጻናቱ በመጠኑም ቢሆን በመስማት ይማራሉ። ሔኖክ ግን በራስ ጥረት የመማርን ሂደት ይከተላል። ተማሪዎቹ በግላቸው ከትምህርቱ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲማሩ የተለያዩ ዓይነት የትምህርት እንቅስቃሴዎችን ያዘጋጅላቸዋል።

እነዚህ ሁለት የመማር ማስተማር አመለካከቶች በሥራ ላይ በሚውሉበት ክፍል ተገኝተህ ነገሩን ተመልክተህ ይሆናል። ቀደም ባለው ጊዜ ዕውቀትን ከአስተማሪው ወደ ተማሪው እንዲዳሰ የማስተላለፍ ስልት ብዙ ሲሠራበት የቆየ ሲሆን ይህ ስልት አሁንም ይሠራበታል። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ አስተማሪዎች የሚከተሉት «በራስ ጥረት መማር» ወይም «ራስን በራስ ማስተማር» የሚለውን ስልት ነው። ይህ የመማር ማስተማር ስልት የተወሰደው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰፊ ጥናት ከተደረገባቸው እንደ ሥነ ልቡና ካሉ የትምህርት ዘርፎች ነው። እንተ እስከ አሁን ድረስ የተማርኸው በዝወራ ስልት ከሆነ ይህ ስልት ዕውቀትን ለማስተላለፍ ጥሩው መንገድ ነው ወይ የሚል ጥያቄ አድሮብህ ይሆናል። በዚህ ዓለም ስንኖር ለሚያሳስቡን ነገሮች መልስ ለመስጠት ብዙ እውነቶችን መማር አስፈላጊ ነው። በዙሪያችን ያለውን ዓለም በንቃት ለመከታተልና በነገር ሁሉ አስተዋይ ሰው ለመሆን እነዚህን ነጥቦች ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ሆኖም ትልቁ ነገር በዚህ ዓለም ስትኖር የተረዳኸውን እውነት ተጠቅመህ በየዕለቱ የሚገጥሙህን ፈተናዎች መፍታት መቻልህ ነው። ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው የተረዳኸውን እውነት በትክክል መጠቀም የምትችለው በመኖር ወይም በመለማመድ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ስለ ማስተማርና ስለ መማር የተሰጡትን ትርጉሞች በቃልህ አጥና። የእነዚህን ቃላት ትክክለኛ ትርጉም በሙከራ ፈተና ስለምትጠየቅ ትርጉማቸውን በሚገባ አስተውል።

1. መማር ማለት በራስ ጥረት (ወይም ራስን በራስ በማስተማር) እውነትን ማወቅና ላወቅነው ነገር ተገቢውን ምላሽ መስጠት ማለት ነው።
2. ማስተማር ማለት ሰዎች እንዲማሩ መርዳት ማለት ነው።

ምናልባት ማስተማርና መማር ተደጋጋፊ ነገሮች መሆናቸውን እያስተዋልህ ላትመጣ አልቀረህም። በአጠቃላይ ሲታይ አንድ ሰው በአግባቡ ካለተማረ ሰዎች ትምህርት ተምረዋል ማለት ነው። ትምህርቱን የሚማሩት ሰዎች በአግባቡ ካልተማሩ ፍሬያማ ትምህርት ተሰጥቷል ማለት አይችልም። ማስተማርና መማር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። አንዱን





ከሌላው ነጥሎ ማየት ከቶ አይቻልም። ከዚህ የተነሣ ይህን ሂደት የመማር ማስተማር ሂደት ልንለው እንችላለን።

(4). ከታች ከተዘረዘሩት ድርጊቶች ፊት ለፊት የዝወራ ትምህርት እንቅስቃሴ ከሆኑ "1" ቁጥር፤ በራስ ጥረት የመማር እንቅስቃሴ ከሆነ "2" ቁጥር ጻፍ።

______ ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በቃል መያዝ
______ ለ. የተለያዩ አመለካከቶችን መወያየት
______ ሐ. ኃሳብን መመርመር
______ መ. ገለጻ መስማት
______ ሠ. ሙከራዎች ማካሄድ
______ ረ. ከጥቁር ሰሌዳ ላይ ትምህርቱን መገልበጥ
______ ሰ. በካርታ ላይ ከተማን መጠቆም
______ ሸ. ታሪክን ማድመጥ

## የተማሪውን አመለካከት መለወጥ

*ዓላማ 2 ትምህርት የሚያመጣውን ውጤትና ለውጥ ለይ።*

አንድ ነገር ለመማር ለውጥ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ተማሪው አንድ እውነት በተረዳ ጊዜ ለዚያ ለተረዳው ነገር ምላሽ ይሰጣል። ተማሪው ለተረዳው ነገር ምላሽ ካልሰጠ፥ ተምሯል ማለት አይችልም፤ እንዲሁም ተማሪው ካልተማረ፥ ትምህርቱ ፍሬያማ አልሆነም።

(5). ማቴ. 28:19-20 አንብብና ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲጠብቁ በሰጠው ትዕዛዝ ውስጥ ምን እንዲያደርጉ አስተማራቸው?

ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ያዘዘውን ነገር ሁሉ «እንዲጠብቁ» በማስተማርና ተማሪዎች አንድን ነገር መማር የሚችሉት ለመለወጥ ፈቃደኛ ሲሆኑ ነው በሚለው መካከል ያለውን ዝምድና አስተዋልህ? አንድ ሰው ኢየሱስ የሰጠውን ትእዛዝ ሳይረዳ እንዴት ሊታዘዝና ሕይወቱን በዚያ ነገር ላይ ሊመሠረት ይችላል? መታዘዝ ማለት የተማርነውን ነገሩን መቀበልና ማድረግ ማለት ነው። ዕውቀት ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ በሥራ ላይ መዋል አለበት። እንግዲህ የመማር ትልቁ ግብ የተማርነውን እውነት በሥራ ላይ ማዋል፥ የተማርነውን እውነት የራሳችን ገንዘብ ማድረግና በተማርነው መሠረት ሕይወታችንን ለመለወጥ ዝግጁ መሆን ነው።

ይህን እውነት መረዳት ክርስቲያናዊ ዕድገትን ለማምጣት በምንሠራው ሥራ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያመጣል። ግባችን ሰዎች በክርስቶስ አድገው እንዲለወጡ መርዳት ነው፤ የክርስቶስ ሕይወት በእነርሱ ሕይወት ውስጥ ሕያው ሆኖ እንዲታይ ማገዝ ነው። ክርስቲያናዊ ምገባ ሰዎች በየጊዜው እየተለወጡ እንዲሄዱና ክርስቶስን እንዲመስሉ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደርጋል። ክርስቲያን በሆንን ጊዜ፥ ሕይወታችን ክርስቶስን ከመምሰል የራቀ ነበር፤ ነገር ግን

የመለወጥና ክርስቶስን የመምሰል ሂደት ነው፤ ሰዎች መንፈሳዊ ብስለትን እንዲያገኙ የመርዳት አገልግሎት ነው።

ልናጠናው የሚገባ አንድ የተገለጠ እውነት አለ። ይኸውም እግዚአብሔር ራሱን በተጻፈ እውነት አማካይነት ገልጾልናል። በክርስቲያናዊ ምገባ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ሁሉ ሰዎች ይህን እውነት ለማወቅ ከፈለጉት፥ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት እንዳለባቸው ማስተማር አለባቸው።

በክርስቲያናዊ ምገባ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሌላው ሊያውቁት የሚገባው ነገር የሰዎች አመለካከት ትልቁን ቦታ የሚይዝ መሆኑን ነው። የአመለካከት ለውጥ ለክርስቲያናዊ ምገባ ትልቅ መሠረት ነው። ኢየሱስ እንዳስተማረው እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ መውደድ የክርስትና መሠረታዊ ባሕርይ ነው። የፈቃድ ነጸብራቅ የሆነው ይህ ፍቅር ባልንጀራን የሚወድ ፍቅር በመጨረሻም ሰውየው ስለ ራሱ ያለውን አመለካከት የሚገልጽ ነው። ፍቅር አመለካከትን ይለውጣል፤ የሰዎች አመለካከት ውስጣቸው በሰረገው ፍቅር ይታወቃል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ስናድግና ክርስቶስን ስንመስል አመለካከታችን የእርሱን አመለካከት ይመስላል።

እንዲሁም ዕውቀትና አመለካከት በራሱ በቂ አይደሉም። ክርስቶስን በሙሉ ልብ መታዘዝ አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ እውነት በምናስተምራቸው ሰዎች ውስጥ ካልታየ ኀላፊነታችንን ተወጥተናል ማለት አይቻልም። በክርስትና ሕይወት ውስጥ ታዛዥነት ትልቅ ቦታ አለው በክርስቲያናዊ ምገባ አገልግሎት ውስጥ ትልቁ ተልዕኮአችን መንፈሳዊ ሕይወትን ማሳደግ በመሆኑ የክርስቶስ ሕይወት በምናገለግላቸው ሰዎች ውስጥ በግልጽ እስኪታይና ባሕርያቸውም የእርሱን ባሕርይ እስኪመስል ድረስ ሰዎችን ልንረዳ ይገባል።

(10). እውነተኛ ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ክርስቲያናዊ ምገባ የሚያደርገው ነገር በቅድሚያ ዕውቀት በመስጠት ለውጥ ማምጣት ነው።
ለ. መማር የእውቀት፣ የአመለካከትና የባህሪ ለውጥን ያጠቃልላል።
ሐ. የምገባ አገልግሎት በብዙ አቅጣጫ ለውጥ ለማምጣት ስለሚፈልግ በአጭር ጊዜ የተገኙ ውጤቶች ይህን ያስገኛሉ።
መ. ክርስቲያናዊ ምገባ ኢየሱስ ባስቀመጠው መንገድ የሚደረግ የሕይወት ለውጥን ያካትታል።
ሠ. ክርስቲያናዊ ምገባ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት መማርን ያጠቃልላል
ረ. እውነት ሕይወት ለዋጭ ኃይል ስለሆነ የለውጥ ፍሳጎት ከተማሪው መምጣት አለበት እንጂ እኛ ተጽዕኖ ማድረግና ለውጥን ማደፋፈር የለብንም።
ሰ. እድገት ለማምጣት ክርስቲያናዊ ምገባን ስናኪያሂድ የኛ ሙከራ የእውቀት ለውጥ ለማምጣት የተቃኘ መሆን አለበት።
ሸ. በክርስቲያናዊ ምገባ ሂደት ውስጥ መማር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የክርስቶስ ባህሪ እንዲገለጥ ያደርጋል።





## የሙከራ ፈተና

1. በዚህ ትምህርት መሠረት የእውቀት፣ የአስተሳሰብና የባህሪ ለውጥ የሚያስገኝ ትምህርት ለመማር ግለሰቡ ትምህርቱን በሕይወቱ ውስጥ በሥራ ላይ ማዋል አለበት፤ ምክንያቱም፦

   ሀ. አንድ ሰው የሚያየውንና የሚሰማውን አልፎ አልፎ ስለሚያስታውስ ነው።
   ለ. ተግባር ከማይጠይቁት ይልቅ ተግባራዊ ምላሽ የሚጠይቁ ትምህርቶች ብዙ ሊታወሱ ይችላሉ።
   ሐ. ሰው ከሚያስበው ይልቅ የሚያደርገው ነገር የበለጠ አስፈላጊ ነው።
   መ. ከሰውየው ማንነት ይልቅ የሚያደርገው ነገር የበለጠ አስፈላጊ ነው።

2. ወንጌልን ለሌላው መናገሩ የአማኙ ኃላፊነት እንደሆነ ቢነገረውና፤ አማኙ ጥሩ ተምሮአል ማለት የሚቻለው፦

   ሀ. ስለ ወንጌል ሥርጭትና ስለ ኃላፊነት ብዙ ካነበበ ነው።
   ለ. ነፍሳትን ስለመማረክና ስለውጤታማ ምሥክርነት ብዙ ሴሚናር ከተካፈለ ነው።
   ሐ. ስለ ኃላፊነቱ የተነገረውን መልእክት በአግባቡ ከተቀበለና በሙሉ ልቡ ከተለማማ ነው።
   መ. አጋጣሚውን በመጠቀም ለማያምን ሰው ስለ ክርስቶስ ከመሰከረ ነው።

3. ኢየሱስ ቤቱን በአሸዋ ላይ ስለ ሰራው ሰነፍ ሰው የተናገረው ምሳሌ (ማቴ. 7፡24-27) ቃሉን ሰምቶ ስለአለመታዘዝ የተነገረ ነው። ይህ የሚያስተምረን፦

   ሀ. ሰዎች ሁሉ የቃሉን እውነት የመረዳት ችሎታ የላቸውም።
   ለ. በአንድ ሰው ውስጥ ጥሩ ለውጥ የሚመጣው የተማረውን እውነት በሕይወቱ ሲተገብረው ነው።
   ሐ. እውቀት ከድርጊት ይልቅ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ነው።
   መ. ድርጊት በእውቀት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑን ነው።

4. የዘወራ ትምህርትን ስልት የሚጠቀሙ አንዳንድ አስተማሪዎች የጥረታቸውን ውጤት የሚመዝኑት ተማሪዎች የተሰጣቸውን መረጃ ያለምንም መዛባት ማስታወስ በመቻላቸው ላይ ተመስርተው ነው። ይህ ምላሽ የትኛውን የመማር ዓይነት ያስታውሰናል።

   | | |
   |---|---|
   | ሀ. አነብናቢ | ሐ. አገናዛቢ |
   | ለ. በራሱ ቋንቋ አብራሪ | መ. በሕይወት ተግባሪ |

5. በጥናታችን መሠረት በራስ ጥረት ስለመማር ትኩረት የማይሰጠው ለየትኛው ነው።

ሐ. የምንማረውን መስማትና መናገር ስንችል ነው።
መ. ተማሪው ሲሰማና በሰማው ላይ ተመርኩዞ ሲያደርግ ነው።

15. ሰዎች እንዴት እንደሚማሩ ባጠናነው ውስጥ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር ሁሉም ተጠቅሰዋል። ያልተጠቀሰው የትኛው ነው?

ሀ. ለውጥ እንዲመጣ ተማሪው በግሉ በትምህርቱ ውስጥ መሳተፍ አለበት።
ለ. ተማሪው አንድን ነገር ልማድ እስኪሆን ድረስ ደጋግሞ በማድረግ በተግባር ይማራል።
ሐ. ተማሪው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲገባ ችግሩን በመፍታት ይማራል
መ. ተማሪው ያለምንም ምሪት በራሱ በመነሳሳት ሲማር የተሻለ ሊያደርግና በፍጥነት ሊማር ይችላል።

16-17. ከታች በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ የትኛው የማስተማር መንገድና የትምህርት ደረጃ በተግባር ላይ እንደዋለ ልብ ብለህ ተመልከት። ከዚያም በትምህርት አቀራረቡ ውስጥ የሚታየውን አዎንታዊና አሉታዊ ሁኔታዎችን በአጭሩ አብራራ። መሻሻል አለበት የምትለውንና ተግባር ላይ የዋለው የትምህርት አቀራረብ እንዳለ ሊቀጥል ይገባል የምትልበትን ምክንያት ልትገልጽ ትችላለህ፡

16. ሮቤል በርካታ አዋቂዎች ያሉበት የሰንበት ትምህርት ክፍል አስተማሪ ነው። በየእሁዱ በክፍል ውስጥ ቆሞ ሲያስተምር የትምህርቱን ይዘት በሚገባ ለመግለጽ ጥሩ ማስታወሻ ይዞ ያቀርባል። ከጥሩ ዝግጅት ጋር በርካታ ምሳሌዎችንና የሕይወት ልምምዶችን በማቅረብ ትምህርቱን ያብራራል። ተማሪዎች የበለጠ እንዲገባቸው ካርታዎችንና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ይጠቀማል። አንዳንድ ተማሪዎች እርሱ ሲናገር ማስታወሻ ይይዛሉ፣ ብዙዎቹ ግን ቀልባቸውን ሰብስበው በፀጥታ ያዳምጣሉ፡ ተማሪዎች ያስተማረውን ትምህርት ያውቃሉ ብሎ ተስፋ ያደርጋል። በየሳምንቱ የሚሰጠው የሙከራ ፈተና ትምህርቱን በሚገባ ለማስታወሳቸው ማስረጃ ነው ብሎ ያምናል። እርሱ የተጠቀመበትን የማስተማር መንገድ በሚገልጸው ፊት ለፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የዝወራ ትምህርት
ለ. በራስ ጥረት መማር
ሐ. መረዳት
መ. በራሱ ቋንቋ አብራሪ
ሠ. አገናዛቢ
ረ. በሕይወት ተግባሪ

17. ሸዋዬ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን መጽሐፍ ቅዱስ ታስተምራለች። ተማሪዎቿ በትልቅ ጠረጴዛ ዙሪያ ይቀመጣሉ፤ በጠረጴዛውም ላይ የጥቅስ ማውጫዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላቶች፣ ካርታዎች፣ ወረቀቶች፣ እርሳሶችና በርካታ የማጣቀሻ መጽሐፍት ተቀምጠዋል። ብዙ ጊዜ ትምህርቱን በአጭሩ ከገለጸችላቸው በኋላ በርካታ ጥያቄዎ ችን በሰሌዳው ላይ ትጽፍላቸዋለች። መልስ እንዲሰጡ በምታበረታታቸው ጊዜም ማንም ከውይይቱ ውጪ እንዳይሆን በጥንቃቄ ትመለከታለች። አብዛኛውን ጊዜ



መማርና ማደግ

ተማሪዎች ከጥናታቸው የተማሩ ትን በራሳቸው ቃላት ይገልጻሉ። ትምህርቱ በአስተሳሰባቸው፤ በስሜታቸውና በባህሪያቸው ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ፤ ያገኙት አዲስ ዕውቀት ከአመለካከታቸው ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ያስረዳሉ። ያገኙትን ዕውቀት በሕይወት ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና የአመለካከት ግምታቸውን ለማስተካከል እንዲጠቀሙበት ይበረታታሉ። ሸዋዬ ጥረቷን የምትመዝነው በምላሻቸው፣ በአመለካከታ ቸውና በባህሪያቸው ላይ በምታየው ለውጥ ነው። ሸዋዬ የምትጠቀምበትን የማስተማር መንገድ በሚገልጸው ፊት ለፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የዝወራ ትምህርት
ለ. በራስ ጥረት መማር
ሐ. መረዳት
መ. በራሱ ቋንቋ አብራሪ
ሠ. አገናዛቢ
ረ. በሕይወት ተግባሪ

18. በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደቀረበው ማስተማር ማለት

ሀ. አንድን ነገር ለሰው መንገር ነው።
ለ. ሰዎችን በሥራ እንዲጠመዱ ወደሚያደርግ እንቅስቃሴ ውስጥ ማስገባት
ሐ. ሰዎች እንዲማሩ መርዳት ነው።
መ. የአንድን ነገር ትክክለኛነትና ተገቢነት ማሳመን ነው።

19. በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደቀረበው መማር ማለት

ሀ. መረጃን ከምንጩ መስማት ነው።
ለ. መረጃ ሲቀርብ ማየትና መስማት ነው።
ሐ. ሰፊ ምርምር አድርጎ እውነቱን ማወቅ ነው።
መ. መረጃን ማወቅና ተገቢውን ምላሽ መስጠት ነው።

20. በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደቀረበው የመማር ግብ

ሀ. በሕይወት ውስጥ የተማርነውን እውነት መሠረት አድርጎ ምርጫን መምረጥና ተግባርን መምራት።
ለ. ለአእምሮና ለማህበራዊ ግንኙነት የሚመች ውሳኔ ለማድረግ መመሪያ ማበጀት።
ሐ. የተሻለና ፍሬያማ ሕይወት ለመኖር የሚያስችል እውቀት፣ አመለካ ከትና ችሎታ ማዳበር።
መ. የሰውን ሁለንተና - እውቀት፣ አመለካከትና ችሎታ ማበልጸግ።

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት አጥንተህ ለትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ፦

- ሰዎች እንዴት እንደሚያድጉ መግለጽና የሰዎች ዐበይት የህይወት ዘመኖች ምን እንደሆኑ መለየት ትችላለህ።
- ተማሪዎች በሕፃንነት ዘመናቸው፥ በወጣትነት ዘመናቸውና በጉልምስና ዘመናቸው የሚያሳዩትን ባሕርያትና በእነዚህ ዐበይት የህይወት ዘመኖች ሥር የሚካተቱትን ንዑስ የህይወት ዘመኖች መግለጽ ትችላለህ።
- በሰዎች ባሕርይ ላይ ተጽዕኖ የሚያመጡ ነገሮችን ዘርዝረህ መናገር ትችላለህ።

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

# የሰዎችን ተፈጥሮአዊ ዕድገት ማወቅ

### ሰዎች እንዴት እንደሚያድጉ መረዳት

*ዓላማ 1 ሰዎች እንዴት እንደሚያድጉ የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

ከሰዎች ጋር የምንመሠርተው ግንኙነትና ሰዎችን ለማሳደግ የምንሰጠው ትምህርት ስለ ሰዎች ተፈጥሮ ባለን ግንዛቤ ላይ በእጅጉ የተመሠረተ ነው። ራሳችንን ለማወቅም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምንረዳቸውን ሰዎች ለማወቅ፥ የሰዎችን ተፈጥሮአዊ ዕድገት ማወቅ ይኖርብናል።

ሰዎች በተለያየ መንገድ ያድጋሉ። ሕይወት ካገኘንበት ጊዜ ጀምሮ በአካል ማደግ እንጀምራለን። ሰውነታችን ለበርካታ ዓመታት ማደጉን ይቀጥላል፤ ይህ ዕድገት እስከ ጉልምስና ዘመን ድረስ ይዘልቃል። ከዚህ በተጨማሪ በአእምሮአዊ፥ በስሜታዊ፥ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ነገሮች እናድጋለን። ሰውነታችን (አካላችን) ዕድገቱን ከጨረሰ በኋላ እንኳ በእነዚህ አራት አቅጣጫዎች እስከ ሕይወታችን ማብቂያ ድረስ ማደጋችንን እንቀጥላለን። ሞት ወይም አርጅና ዕድገታችንን ካላደናቀፈው በቀር በአራቱም አቅጣጫ እስከ መጨረሻው እናድጋለን።

በእነዚህ አምስት አቅጣጫዎች ማደግ በጣም አስፈላጊ ነው። በእነዚህ አምስት አቅጣጫዎች ተገቢውን ዕድገት ማግኘት ማለት ሙሉ ሰው መሆን ማለት ነው። ሙሉ ሰው ለመሆን በሁሉም አቅጣጫዎች እኩል የሆነ ዕድገት ማግኘት ያስፈልጋል። በሁሉም አቅጣጫዎች እኩል ያላደገ ሰው በሕይወቱ ብዙ ቀውስ





ይገጥመዋል፤ በአንዱ አቅጣጫ አድጎ በሌላ አቅጣጫ ያላደገ ሰው ሚዛናዊ ሕይወት መኖር አይችልም። የክርስቲያናዊ ምግባ ግብ ሰዎችን ሙሉ ሰው ማድረግ፤ አንድን ሰው በእያንዳንዱ የህይወት አቅጣጫ ማሳደግ የክርስቲያናዊ ምግባ አንዱ ግብ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖች ለመንፈሳዊ ዕድገት ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ። በክርስቶስ ያገኘነው ሕይወት ዘላለማዊ በመሆኑ ለመንፈሳዊ ዕድገት የምንሰጠው ቦታ ከምንም የላቀ ነው። ሌላው የህይወት አቅጣጫ ጊዜያዊና ሞት በመጣ ጊዜ የሚያከትም ነው፤ ነገር ግን የሰው መንፈስ ከሞት በኋላ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል። ስለዚህ በክርስቲያናዊ ምግባ አገልግሎት ውስጥ ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የምንሰጠው ቦታ ከፍተኛ ነው።

ዕድገት ቀስ በቀስ የሚመጣ ነገር በመሆኑ በአንድ ጊዜ ሙሉ ሰው መሆን እንደማይቻል መገንዘብ ተገቢ ነው። ዕድገት እንዲኖር ከተፈለገ ምግባ ያስፈልጋል። አስተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች ክርስቲያኖች ለመንፈሳዊ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ለማድረግ ሰፊ ዕድል አላቸው።

(1). እውነት ከሆኑት ዐረፍተ ነገሮች ፊት ያሉትን ፊደላት አክብብ።

ሀ. ሰዎች በአካል፣ በአእምሮ፣ በስሜት፣ በማህበራዊና በመንፈሳዊ ሕይወት ያድጋሉ።
ለ. በሁሉም አቅጣጫ ማደግ ለክርስቲያን አስፈላጊ ነው።
ሐ. ሙሉነት የሚገኘው ሰው ሊያድግባቸው በሚችልባቸው አቅጣጫዎች ሚዛናዊ ዕድገት ሲኖር ነው።
መ. ክርስቲያናዊ ምግባ ለአካላዊ እድገት ቅድሚያ ይሰጣል።
ሠ. ክርስቲያናዊ ዕድገት ተፈጥሮአዊና በራሱ የሚመጣ ነው።
ረ. ከአካል ዕድገት በቀር ሌላው ሁሉ በሕይወት ዘመን ሁሉ መቀጠል አለበት።

### ዐበይት የህይወት ዘመኖች

*ዓላማ 2 የህይወት ዘመን ዕድገቶችን በትክክል ለይ።*

ሦስት ዐበይት (ዋና ዋና) የህይወት ዘመኖች እንዳሉ ይታወቃል፤ እነርሱም *የሕፃንነት ዘመን፥ የወጣትነት ዘመንና የጉልምስና ዘመን* ናቸው። የሕፃንነት ዘመን የሚባለው፥ አንድ ሰው ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሥራ አንድ ወይም አሥራ ሁለት ዓመት ድረስ ያለው የዕድሜ ክልል ነው። የወጣትነት ዘመን የሚባለው፥ ከአሥራ ሁለት ዓመት እስከ አሥራ ስምንት ወይም አሥራ ዘጠኝ ዓመት ድረስ ያለው የዕድሜ ክልል ነው። የጉልምስና ዘመን የሚባለው ደግሞ ከሃያ ዓመት አስከ ሞት ድረስ ያለው የዕድሜ ክልል ነው ሲሆን፥ ይህ የህይወት ዘመን ከሌሎቹ የህይወት ዘመኖች ሁሉ በጣም ረጅም ነው። ብዙ ሰዎች ረጅም ዘመን ስለሚኖሩ፥ ይህ የህይወት ዘመን፥ አንድ ሰው በአጠቃላይ ከሚኖረው ዘመን ሁለት ሦስተኛውን ወይም ሦስት አራተኛውን ይይዛል።

በአካባቢያቸው ላለው ሕይወት እንግዳ በመሆናቸው ሁልጊዜ ጠያቂ ፍጡራን ናቸው። በዙሪያቸው ያለውን ዓለም የሚያጠኑትና የሚያስሱት በዚህ መልክ ነው።

በዚህ ወቅት ሕፃናት ሐሳባቸውን ለመግለጽ ቋንቋ የሚማሩበት ወቅት ነው። የመጀመሪያዋን ቃል ከተናገሩበት ጊዜ ጀምሮ ቋንቋን የመጠቀም ችሎታቸው ፈጣን ዕድገት ያሳያል። ሕፃኑ ትምህርት ቤት ሲገባ ወደ 1,000 የሚጠጉ ቃላትን ያውቃል፤ ይህ ችሎታ ሕፃኑ በሚያድግበት አካባቢና ባሕል የተወሰነ ነው። ሕፃናት ቋንቋን የሚጠቀሙት ለመነጋገሪያ ብቻ ነው። ማንበብና መጻፍ ገና አልተማሩም። በዚህ ዕድሜ ላይ ያሉ ሕፃናትን ለማስተማር ሕፃናቱ የሚያውቁትን ቋንቋ መጠቀም አስፈላጊ ነው። የሚነገራቸውን ነገር ሁሉ የሚረዱት በመጠኑ ነው፤ ስለዚህ ለማለት የምንፈልገውን ነገር በትክክል የሚገልጹ ቃላትን ብቻ መጠቀም ተገቢ ነው።

በዚህ ቀዳማይ የዕድገት ዘመን፥ ሕፃናት በአንድ ሐሳብ ላይ ያላቸው ትኩረት በጣም ውሱን ነው። በሁለትና በሦስት ዓመት ዕድሜ ላይ ያሉ ሕፃናት በአንድ ሐሳብ ላይ የሚያተኩሩት ለሁለት ወይም ለሦስት ደቂቃ ብቻ ነው፤ ሆኖም ትምህርት ቤት መሄድ ሲጀምሩ በአንድ ሐሳብ ላይ የማተኮር ችሎታቸው ወደ ለባትና አሥር ደቂቃ ከፍ ይላል። ከዚህ የተነሣ አስተማሪዎች የሚያስተምሩትን ነገር፥ ሕፃናት በአንድ ሐሳብ ላይ ለማተኮር ከሚችሉበት ጊዜ ጋር ማስማማት አለባቸው። የተማሪዎቹ ሐሳብ ወደ ሌላ ነገር ላይ ከመዞሩ በፊት የሚማሩትን ነገር መለወጥ ያስፈልጋል።

አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናት አላሚ ፍጡራን ናቸው። በዙሪያቸው ያለውን ገሃድ ዓለም ረስተው በሕልም ዓለም ለመኖር ትልቅ ችሎታ አላቸው። ይህን ባሕርያቸውን በመጠቀም ብዙ ቁም ነገሮችን ማስተማር ይቻላል። በዚህ የህይወት ዘመን በርካታ ወላጆች፥ ልጆቻቸው ቀላል መዝሙሮችንና አጭር ጥቅሶችን በቃላቸው እንዲያጠኑ ያበረታቱአቸዋል። ሕፃናት በዚህ የህይወት ዘመን የሚያሳዩት ክህሎት በጣም አስገራሚ ነው፤ ምክንያቱም የተማሩትን ነገር በቀላሉ ለመያዝ ትልቅ ችሎታ አላቸው፤ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ፍላጎታቸው በጣም ከፍተኛ ነው።

በዚህ ቀዳማይ ዘመን ሕፃናት ቤተሰቦቻቸው ባሉበት ሰፍራ ድፍረት ይሰማቸዋል፤ የሚያስፈራቸውና የሚያስሰባቸው ነገር የለም። ሆኖም የማያውቁት ሰው ሲያዩ ይፈራሉ። ለእነርሱ እውነተኛ ወዳጅ በመሆን ፍርሃታቸውን እንዲተዉ ማድረግ ይቻላል።

## መንፈሳዊ ዕድገት

በዚህ ቀዳማይ የህይወት ዘመን ሕፃናት የተነገራቸውን ነገር ሁሉ ያምናሉ፤ ደግሞም ማንም ሰው በቀላሉ ሊያታልላቸው ይችላል። ሕፃናት ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ወደ ኋላ አይሉም፤ በተለይ ደግሞ ፍቅርና ወዳጅነት ካሳየናቸው የምንለውን ነገር በደስታ ያደርጉታል። ሕፃናት እግዚአብሔርን ለመረዳት ያላቸው ችሎታ ውሱን ቢሆንም፥ መሠረታዊ መንፈሳዊ እውነቶችን





መረዳት ይችላሉ። እግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ መሆኑን፥ ቤተክርስቲያን የተለየ ሰፍራ መሆኑን፥ እንዲሁም እግዚአብሔር የሚወዳቸውና የሚያስብላቸው አምላክ መሆኑን መረዳት ይችላሉ። ደግሞም ስለ እግዚአብሔር ከተማሩት ነገር በመነሣት እግዚአብሔርን ማምለክ ይችላሉ። መሠረታዊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በቀላሉ በቃላቸው መያዝ ይችላሉ። ለተረዱት ፍቅር ምላሽ መስጠትና ለእግዚአብሔር ፍቅር አጸፋውን መመለስ ይችላሉ።

(9). በቀዳማይ የህፃንነት ዘመን ካሉ ተማሪዎች ጋር የሚስማማውን እንቅስቃሴ የሚያመለክቱትን ፊደሉን በመከበብ አመልክት።

ሀ. ስለ እግዚአብሔር በደስታ መዘመር።
ለ. በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ሁሉ በጸጥታ እንዲቀመጡ ማዘዝ።
ሐ. ልጆቹ ጊዜያቸውን ሁሉ ከሌሎች ጋር እንዲጫወቱ ይፈለጋል።
መ. እንቅስቃሴ ያለበትን ተግባር በማካከል በየመሐሉ አጠር ያለ የጸጥታ ትምህርት ጊዜ ማድረግ።
ሠ. ልጆች ገና ትንንሽ ህጻናት በለሆኑ ስለ እግዚአብሔር ልንነግራቸው አይገባም።
ረ. ልጆቹ ለተወሰነ ጊዜ በትምህርቱ ጎን ለጎን እንዲጫወቱ መፍቀድ።
ሰ. ልጆቹ በአይናቸው እንዲያዩት በእጃቸው ግን እንዳይደርሱበት ዕቃዎቹን በከፍታ ሥፍራ ማስቀመጥ።
ሸ. እግዚአብሔርን እንደ አፍቃሪ ጓደኛ አድርጎ ማቅረብ።
ቀ. የጌታን ጸሎት በቃላቸው እንዲይዙ ማስተማር።
በ. ከትምህርቱ ጋር የሚሄዱ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ልጆቹ እንዲነካኩት መፍቀድ።

10. በሦስትና በስድስት ዓመት እድሜ ክልል መካከል ያሉ ሕጻናትን ልብ ብለህ ተመልከት። ስለ እነርሱ ያስተዋልከውን ባህርያት በማስታወሻ ደብተርህ በመጻፍ በዚህ ትምህርት ከተማርከው ጋር አነጻጽር።

## መካከለኛ የሕፃንነት ዘመን

ሕፃናት መደበኛ ትምህርት ሲጀምሩ ከቀዳማይ የሕፃንነት ዘመን ወደ መካከለኛ የሕፃንነት ዘመን ተሸጋግረዋል ማለት ነው። ይህ ወቅት በሕፃናት ሕይወት ላይ አያሌ ዕድገት የሚታይበት ወቅት ነው፤ በሕፃናት ላይ የሚታየው ዕድገት አሁንም ፈጣን ነው።

## አካላዊ ዕድገት

በመካከለኛ የሕፃንነት ዘመን ሕፃናት በጣም ፈጣን ናቸው። ሩጫና ዝላይ የበዛበትን ጨዋታ በጣም ይወዳሉ፤ ሆኖም ቶሎ ይደክማቸዋል። ያላቸው ኀይል (ጉልበት) ሁሉ የሚውለው ለዕድገት ነው። አካላዊ ዕድገታቸው አንድ ወጥ (ኢደንባዊ/ ኢመደበኛ) አይደለም። በአንድ ወቅት ፈጣን ዕድገት ያሳያሉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀስ ብለው ያድጋሉ። በዚህ ወቅት ሌላው አካላቸው ፈጣን

(12). በስድስትና በዘጠኝ ዓመት ዕድሜ መካከል ያሉ ሁለት ወይም ሦስት ህጻናትን በጥንቃቄ ተመልከት። ያስተዋልከውን ባህሪያት በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር። በዚህ ክፍል ከተማርከው ትምህርት ጋርም አነጻጽረው።

### ዳኅራይ የሕፃንነት ዘመን

ከወጣትነት ዘመን በፊት ያለ ሕይወት በጣም የሚያስደስትና ብዙ ፈተና የበዛበት ሕይወት ነው። ልጆች በየትኛውም የህይወት አቅጣጫ ያላቸው ክህሎት እጅግ ትልቅ ነው። በጣም ፈጣንና በጥባጭ ናቸው፤ ሕይወት ለእነርሱ በኳር ናት። ፍላጎታቸውና ምኞታቸው ብዙና ልዩ ልዩ ነው።

### አካላዊ ዕድገት

በዳኅራይ የሕፃንነት ዘመን ሕፃናት የማይደክም ጉልበት አላቸው። አሁን በቀዳማይ የሕፃንነት ዘመን ከነበራቸው ይልቅ የበለጠ ጉልበት አላቸው፤ ሆኖም አካላዊ ዕድገታቸው ከቀድሞው ዝግተኛ ነው። ጥሩ የምግብ ፍላጎት በላላቸው ብዙ ምግብ ይበላሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ የፀሐይ ብርሃን፣ ንጹሕ አየርና ዕረፍት ይፈልጋሉ። የጡንቻቸው ዕድገት ከምንጊዜውም ይልቅ የተሻለ በለሆነ በጣም ረቂቅ የሆኑ ሥራዎች ለመሥራት ብቁ ናቸው። በዚህ ወቅት ለሰውነት ንጽሕና የሚሰጡት ቦታ ዝቅተኛ ነው። ከዚህ የተነሣ ለግል ንብረቶቻቸው ጥንቃቄ አያደርጉም፤ ልብሶቻቸውን፣ መጽሐፎቻቸውንና ሌሎችንም ዕቃዎች በጥንቃቄ አይዙም። ተገቢ ምክርና ምሪት ከተሰጣቸው ጉልበታቸውን ፍሬና ጥቅም ላለው ነገር ማዋል ይቻላል።

### አእምሮአዊ ዕድገት

በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሕፃናት በጣም ጠያቂና መርማሪ ናቸው። በትክክል ማሰብና ማሰላት የሚጀምሩበት ወቅት ነው። አዳዲስ እውነቶችን ለመማር ንቁና ፈጣን ናቸው። የተለያዩ ነገሮችን መሰብሰብ በጣም ያስደስታቸዋል፤ ከመጻሕፍትና ከማስታወቂያዎች ላይ የተለያዩ ሥዕሎችን እንዲሁም ቴምብሮችን፣ ቆርኪዎችን፣ ድንጋዮችንና ነፍሳትን (እንደ ቢራቢሮ ያሉ) መሰብሰብ ይወዳሉ። ለነገሮች ያላቸው ግምት ወደ ፈጠራ ያመራቸዋል፤ በመሆኑም ከወረቀትና ከወዳደቁ ዕቃዎች የተለያዩ የመጫወቻ መሣሪያዎች ይሠራሉ። አብዛኛውን ጊዜ ቀላል ንባብና ጀብዱ የተሞላበት ታሪክ ይወዳሉ። ስለ ሚሲዮናውያን የተጻፉ መጻሕፍትና አዳዲስ ቦታዎች ስሜታቸውን ይነካዋል። በዚህ የህይወት ዘመን የሚገኙ ሕፃናት አብዛኛውን ጊዜ ከታሪኩ ዋና ገፀ ባሕርይ ጋር ራሳቸውን ያስተያያሉ። አንድን ነገር በቃላቸው ቶሎ የማጥናትና ረቂቅ እሳቤዎችን የመረዳት ችሎታ አላቸው። ሙሉ በሙሉ ባይረዱትም እሳቤዎችን መልሶ የመናገር ችሎታ አላቸው። ራሳቸውን እያወቁ ቢመጡም ስሜታቸው ስስ ነው፤ በመሆኑም ፈጥነው እጅ ይሰጣሉ። ለመከራከርና ለመጨቃጨቅ ፈጣን ናቸው፤ ቶሎ ይረበሻሉ፤ ሆኖም ፈጥነው ይበርዳሉ፤ ቂም መያዝ የሚባል ነገር አያውቁም። በዚህ የህይወት ዘመን ውስጥ





የሚገኙ ልጆች ውሉን በሆኑ መረጃዎች ላይ ቆመው ውሳኔ ለመስጠት ጊዜ አይወስድባቸውም። ወደ ውሳኔ ከመምጣታቸው በፊት በቂ መረጃ እንዲያሰባስቡ ልናስተምራቸው ይገባል።

በዳኅራይ የሕፃንነት ዘመን ሕፃናት በአብዛኛው ስስ ባሕርይ (ቶሎ የማዘን፣ የመቆጣት፣ የመበሳጨት፣ የመወሰድ) አላቸው፤ ደፋር ቢመስሉም ፈሪ ናቸው። እውነተኛ ስሜታቸውን ይደብቃሉ። ጨዋታና ቀልድ በጣም ይወዳሉ፤ ለሚያዩትና ለሚሰሙት ቀልድ ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ።

### ማኅበራዊ ዕድገት

በዚህ የህይወት ዘመን የሚገኙ ሕፃናት የወላጆቻቸውን እርዳታ ፍለጋ ዘወትር ወደ ወላጆቻቸው ቢሮጡም ከጥገኝነት ነጻ ለመውጣት ግን ይፈልጋሉ። በእነርሱ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ምን እንደሚፈልጉ ያውቃሉ፤ ማለትም በእነርሱ የዕድሜ ክልል ባሉ ሕፃናት ዘንድ ታዋቂ የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ያውቃሉ። ካገኙት ኅብረት ጋር ለመቀላቀል ጊዜ አይወስድባቸውም፤ በእነርሱ የዕድሜ ክልል ያሉ ሕፃናትን የሚያቅፍ ቡድንና ክበብ ማደራጀት ይሆንላቸዋል። ሰዎችን ያደንቃሉ፤ የሚያደንቋቸውን ሰዎች ይከተላሉ። ከጎልማሳ መሪ ይልቅ በእነርሱ ዕድሜ ከሚገኙ ሕፃናት ጋር ውድድር በጣም ይወዳሉ፤ የቡድንም ሆነ የግል ውድድር እጅግ ያስደስታቸዋል። በማንኛውም ነገር ውስጥ የሚሳተፉት በሙሉ ስሜት በመሆኑ ውጤቱን የሚጠባበቁት በናፍቆት ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት የጾታ ልዩነት በጉልህ ይስተዋላል። ለምሳሌ ሴቶች፣ ወንዶች ባሉበት ቡድን (ክበብ) ውስጥ መግባት አይችሉም።

### መንፈሳዊ ዕድገት

በዚህ የህይወት ዘመን የሚገኙ ሕፃናት «ጀግና አምላኪ» በመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የእምነት አባቶችን ታሪክ እንዲያጠኑ መደረግ አለበት። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጆች በአብዛኛው ጌታን ለመቀበል ዝግጁ ናቸው፤ ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሊያፈርሱ አይችሉም የሚል እምነት ሊያድርብን አይገባም። በዚህ ወሳኝ የህይወት ዘመን ስለ እግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅድ፣ ስለ ኃጢአትና ኃጢአትን ተናዞ ይቅርታ ስለ ማግኘት ብዙ ልናስተምራቸው ይገባል። መንፈሳዊ ትምህርቶች፣ የቤተክርስቲያን አስተምህሮዎችን፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባርንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን የማስተማሪያው ትክክለኛ ጊዜ ይህ ጊዜ ነው። ምክንያቱም አዳዲስ እውነቶችን ለመጨበጥ በሚያስችል መልኩ የቀረበላቸውን መንፈሳዊ እውነት በምሳሌና በአብነት ተደግፎ ከቀረበላቸው በሚገባ ያስተውሉታል። ጥቅሶችን እንዲያጠኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና መጸለይ አስፈላጊ መሆኑን በአንጽንዖት መንገር ተገቢ ነው፤ እንዲሁም ክርስቶስን መምሰልና ማገልገል በትልቁ ሊያስቡበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

(13). ከዳህራይ የህጻንነት ዕድሜ ዘመን አንጻር ለክርስቲያናዊ ምግባ ጥሩ አጋጣሚ የሆነው የትኛው ነው።

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ወጣ ብለው በክረምት የሚሰባሰቡበት ፕሮግራም።
ለ. መጽሐፍ ቅዱስን በቃል የሚያጠኑበት ክለብ።
ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ለለመጻፉ ተከታታይ ገለጻ ማቅረብ።
መ. የቤተ ክርስቲያን አለተምህሮ የሚጠናበት ክፍል።
ሠ. ጠቃሚና አበደሳች ታሪኮችን የያዙ መጻሕፍት ያሉበት ቤተ መጻ ሕፍት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማቋቋም።
ረ. የልጆች የወንጌል ሥርዓት ትልቅ ስብሰባ።
ሰ. የአልኮል መጠንን ጉዳት በተመለከተ የፓናል ውይይት ማዘጋጀት።

(14). በአሥርና በአሥራ ሁለት ዓመታት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሁለት ወይም ሦስት ልጆችን ልብ ብለህ ተመልከት። በማስታወሻ ደብተርህ የተመለከትከውን ባህርያት ከጻፍክ በኋላ በዚህ ትምህርት ውስጥ ከተገለጸው ጋር አወዳድረው።

## የወጣትነት ዘመን

በሕፃንነት ዘመን ሰዎች የሚያሳዩትን ለውጥና ዕድገት በቀላሉ መለየት ይቻላል፤ በተለይ ደግሞ በመካከለኛና በዳኅራይ የሕፃንነት ዘመን ከሚታየው ለውጥና ዕድገት ይልቅ በቀዳማይ የሕፃንነት ዘመን የሚታየውን ለውጥና ዕድገት በቀላሉ ማስተዋል ይቻላል። በወጣትነት ዘመን ሰዎች ምንም እንኳ በተመሳሳይ የዕድሜ ደረጃ ላይ ቢሆኑም በአካላዊ፥ በማኅበራዊ፥ በመንፈሳዊና በአእምሮአዊ የሚያሳዩት ዕድገት ከሰው ሰው ይለያያል። በተመሳሳይ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወጣቶች በተመሳሳይ መንገድ ባሕርያቸውን ይገልጻሉ ብሎ መናገር በጣም ያለችግራል። ይህን የዕድገት ደረጃ ስናጠና በተወሰነ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚከሰተውን ውሉን ለውጥ ትተን በአጠቃላይ የዕድገት አኪያሄድ ላይ ብቻ እናተኩራለን። እርግጥ ነው በተመሳሳይ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወጣቶች በርካታ ተመሳሳይ ነገር አላቸው፤ ሆኖም በሕፃንነት ዘመን ከሚታየው ይልቅ በወጣትነት ዘመን የሚታየው ልዩነት ትልቅ ነው።

## *ቀዳማይ የወጣትነት ዘመን*

የወጣትነት ዘመን ከሕፃንነት ዘመን ወደ ጉልምስና ዘመን መሸጋገሪያ ነው። በወላጆች ላይ ጥገኛ ከመሆን ራስን ወደ መቻል እንዲሁም እንደ ሕፃን በሌላ ሰው ከብካቤ ሥር ከመሆን በራስ ሐሳብና ውሳኔ መመራት የመሸጋገሪያ ዘመን ምልክት ነው።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፥ ቀዳማይ የወጣትነት ዘመን ከአሥራ ሁለት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ድረስ ያሉትን ወጣቶች ያካትታል። ይህ





ዕድሜ ትልቅ ለውጥ የሚታይበት ዕድሜ ነው፤ በተለይ ደግሞ በአካላዊና በማኅበራዊ ሕይወት ረገድ ከፍተኛ ለውጥ የሚከሰትበት ዕድሜ ነው። በብዙ አገሮች እንደሚታየው፥ በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው።

## *አካላዊ ዕድገት*

ወጣቶች በአካል ያድጋሉ። ወጣት ሴቶች በቀዳማይ የወጣትነት ዘመን በጉልምስና ዘመን የሚኖራቸውን ቁመት ይይዛሉ። ወጣት ሴቶች በዚህ የዕድሜ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ዕድገታቸው ከወጣት ወንዶች ከሁለት እስከ አራት ዓመት ይቀድማል። በዚህ ወቅት ዐበይት የሆኑ የሰውነት ክፍሎቻቸው ያድጋሉ፤ ልባቸው በሁለት እጥፍ ያድጋል፤ ሳንባቸው ያድጋል፤ ዕጢዎቻቸው ሥራቸውን አቀላጥፈው መሥራት ይጀምራሉ። የአጥንታቸው ዕድገት ከዕድሜያቸው ዕድገት ጋር ስለማይመጣጠን ቅርጻቸው ላይስተካከል ይችላል፤ ይህም ያሳፍራቸዋል። የወጣቶች ሀብለ ድምፅ ስለሚጎረንን አብዛኛውን ጊዜ ድምፃቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው ይታያል።

በቀዳማይ የወጣትነት ዘመን ለአካል መጠን መድረስን የሚያሳዩ ምልክቶች መታየት ይጀምራሉ። በዚህ ወቅት የሩካቤ ሥጋ ዕጢዎች ያድጋሉ፤ እንዲሁም ለሩካቤ ሥጋ ብቁ የሚያደርጉ የአካል ክፍሎች ያድጋሉ። የወጣት ሴቶች አካላዊ ቅርጽ በጉልምስና ዘመን የሚኖራቸውን አካላዊ ቅርጽ ይይዛል፤ የወጣት ወንዶች አካላዊ ቅርጽ ደግሞ ተባዕታዊ ቅርጹን ይይዛል። በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ውስጥ ከሕፃንነት ወደ ወጣትነት መሸጋገራቸውን ለማሳየት የተለዩ ሥርዐቶችን ያደርጋሉ፤ ወይም የንባብ ክፍሎችን ያነባሉ።

## *አእምሮአዊ ዕድገት*

የወጣቶች የማሰብ ክህሎት ያድጋል። ጥልቅ ሐሳቦችን ለማሰብ ብቁ ናቸው፤ ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ ተቺና ተጠራጣሪ ናቸው። ይህም የራሳቸውን ነጻ ሐሳብ ለማሰብ የሚያስችል ትልቅ ዕድገት ነው። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች/ ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ሲሉ ራሳቸውን በብዙ ነገር ይጎዳሉ። አብዛኛውን ጊዜ ከህሎታቸውን፥ መልካቸውን፥ አካባቢያቸውን፥ ቤተሰባቸውን ወይም ለየት የሚያደርጋቸውን ግላዊ ነገሮቻቸውን አይቀበሉትም። ስለ ራሳቸው ባላቸው አመለካከት ላይ ለውጥ እንዳላቸው ያስተውሉታል። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች አእምሮአቸውን በሚገባ መጠቀም ስለሚጀምሩ ሐሳባዊነት ያጠቃቸዋል፤ በሌላ አነጋገር ሕልመኞች ናቸው።

## *ማኅበራዊ ዕድገት*

በቀዳማይ የወጣትነት ዘመን ወላጆች በልጆቻቸው ላይ የሚኖራቸው ተጽዕኖ (ቁጥጥር) ስለሚቀንስ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት የላላ ይሆናል። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ተቀባይነትን በእጅጉ ይሻሉ። ዝነኛ መሆን ትልቁ ምኞታቸው ነው። ሕይወት ስትጠነክርባቸው ቁጡ

ይሆናሉ። ሆኖም ራሳቸውን ነጻ ለማውጣትና ከእኩዮቻቸው ጋር የሰመረ ግንኙነት ለመፍጠር በሚያደርጉት ትግል ውስጥ ብቸኞች ይሆናሉ። በዚህ ጊዜ የሚወዳቸውንና የሚያስብላቸውን ሰው ከምንጊዜውም በላይ ይሻሉ። የበሰሉና የህይወትን ትግል ያሸነፉ ሰዎች የእነርሱን ትግል እንዲያውቁላቸው ይመኛሉ፤ በተለይ ደግሞ ወላጆቻቸው እንዲረዱአቸው ይፈልጋሉ። ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ የማይሆን ነገር ውስጥ ይገባሉ፤ እንዲሁም እኩዮቻቸው የሚያደርጉትን ነገር (ለምሳሌ አደንዛዥ ዕጾችን መውሰድ፥ ከተቃራኒ ጾታዎች ጋር ወዳጅነት መመሥረት፥ መጠጣት) እነርሱም ያደርጋሉ። አዳዲስ ነገሮችን ለማየት ከሚያድርባቸው ጉጉት የተነሣ ሐሰተኛ ትምህርት ውስጥ ይገባሉ፤ ኢክርስቲያን የሆነ ትምህርት ይከተላሉ። ይህ ዕድሜ በወጣቶቹም ሆነ ለቤተሰብና ለኅብረተሰብ ወሳኝ ዕድሜ ነው።

### መንፈሳዊ ዕድገት

በቀዳማይ የወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች በሕይወታቸው የሚገጥማቸው ተስፋ መቁረጥና ጥርጣሬ በመንፈሳዊው ዓለም ሊታይባቸው ይችላል። ራሳቸውን የሚጠሉ ወጣቶች እነርሱን የፈጠረ እምላክ ሰዎች የሚወድና ለሰዎች የሚያስብ እምላክ መሆኑን መቀበል ያዳግታቸዋል። በዚህ ዕድሚ ላይ ልዩ ክብካቤና ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል። ወላጆችና አስተማሪዎች እንደ ባሕርያቸው ወይም እንደ ማንነታቸው ሊቀበሏቸውና ወጣቶች ሊታመኑባቸው በሚችል መልኩ ግንኙነት መመሥረት ይኖርባቸዋል። በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ ከእነርሱ ጋር ስትገናኝ በትግላቸው ወቅት ብቻቸውን መጓዝ እንደ ሌለባቸው ልታስተምራቸው ይገባል። ሕይወታቸውን ለኢየሱስ ከሰጡ የድል ሕይወት እንዲኖሩ የእርሱን ኀይል ሊሰጣቸው እንደሚችል አሳያቸው፤ ኢየሱስ ሊያጽናናቸውና ከጎናቸው ሆኖ ሊረዳቸው ዘወትር ዝግጁ እንደሆነ ግለጥላቸው። በሕይወታቸው የሚገጥማቸውን ችግር ከመጽሐፍ ቅዱስ መርሆዎች አኳያ እንዲያጤኑት እሳስባቸው።

### መካከለኛ የወጣትነት ዘመን

መካከለኛ የወጣትነት ዘመን ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ አሥራ ስምንት ዓመት ድረስ ያሉትን ያካትታል። በብዙ አገሮች በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ በከተማ አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ናቸው። በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች ደግሞ ቤተሰቦቻቸ ውን ለመርዳት በጉልበት ሥራ ላይ ይሰማራሉ። አራት የዕድገት ዐይነቶችን እንመለከታለን።

### አካላዊ ዕድገት

በመካከለኛ የወጣትነት ዘመን ላይ የሚገኙ ወጣቶች ማደጋቸውን ይቀጥላሉ። በአጠቃላይ ሲታይ ወጣት ሴቶች በጉልምስና ዘመን ከሚኖራቸው ቁመት ላይ ሲደርሱ ወጣት ወንዶች ደግሞ በመካከለኛ የወጣትነት ዘመንም ሆነ በዳኅራይ የወጣትነት ዘመን ማደጋቸውን ይቀጥላሉ። ወጣት ወንዶችም ሆኑ ወጣት





ሴቶች በአካላዊ ዕድገታቸው ላይ ለውጥ ያሳያሉ። ወጣት ወንዶች ጡንቻቸው ያድጋል። ከወጣት ሴቶች የተሻለ ጉልበትና ጽናት አላቸው። ወጣት ወንዶች ጢም ማብቀል ይጀምራሉ፤ ወጣት ሴቶች በእንስታዊ ገጽታ ማደጋቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ዕድሚ ላይ የሚገኙ ወጣቶች እንቅስቃሴ የበዛበት ተግባር በጣም ይወዳሉ፤ በፈቃደኝነት በሚሳተፉበት ተግባር ላይ መልካም አቋም ያሳያሉ። ወጣት ወንዶችም ሆኑ ወጣት ሴቶች ስለመልካቸውና ላሰባበሳቸው ይጨነቃሉ፤ ከዚህ የተነሣ ራሳቸውን በማስማመር ብዙ ጊዜ ያጠፋሉ።

### አእምሮአዊ ዕድገት

በቀዳማይ የወጣትነት ዘመን ላይ የነበራቸው ብርቱ የማሰብ ችሎታ በመካከለኛ የወጣትነት ዘመን የበለጠ እየበሰለ ይሄዳል። የአስተሳሰብ ክህሎታቸውና ብያኔአቸው ያድጋል። ሌሎች ሰዎች የሚሰጡአቸው መልስ አያጠግባቸውም። ወጣቶች የራሳቸውን አእምሮአዊ ችግር ራሳቸው መፍታት አለባቸው። በዚህ ጊዜ ወደፊት መሆን በሚፈልጉት ነገር ላይ ማተኮር ይጀምራሉ።

በሕልም ዓለም የመኖር ባሕርያቸው አሁንም እንዳለ ነው። ብያኔአቸው በአብዛኛው የሚመሠረተው ለእነርሱ አመክንዮአዊ በሚመስላቸው ነገር ላይ ነው። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች በእነርሱ ሐሳባዊና ሕልማዊ ሐሳብና በዓለም ውስጥ በሚገጥማቸው እውናዊ ነገር መካከል ልዩነት ለማድረግ ያቅታቸዋል።

### ማኅበራዊ ዕድገት

ማኅበራዊ አስተሳሰባቸው የሚያድገውና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ደፋ ቀና የሚሉት በዚህ ዕድሜ ላይ ነው። በኅብረተሰቡ ውስጥ የእነርሱ ቦታ ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አላቸው። ራሳቸውን ከሌለው ነጥለው መመልከት ይጀምራሉ። ይህም ራሳቸውን ልዩ አድርገው እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። እያንዳንዱ ወጣት ራሱን ከሌላው የሚለየው ምን እንደሆነ እየተገነዘበ ይመጣል፤ ለምሳሌ እነርሱ የሚወዱትና የሚጠ ሉት ምን እንደሆነ፥ የእነርሱ ችሎታ፥ ግብ፥ ምኞትና ሕይወታቸውን የሚመሩበት አቅጣጫ ምን እንደሆነ ያውቃሉ።

በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ስለ ወደፊት ዕጣ ፈንታቸው በጣም ይጨነቃሉ። ይህም ለእነርሱ አዲስ ሕይወት ነው። በዚህ የሽግግር ወቅት ባሕርያቸው ተለዋዋጭና የማይጨበጥ ሊሆን ይችላል።

### መንፈሳዊ ዕድገት

ለሁሉ ነገር መልስ የሚፈልገውና ስል የሆነው የወጣቶች ኅሊና አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን መኖር ሊጠራጠር ይችላል። «የመኖር ትርጉሙ ምንድን ነው?» «እግዚአብሔር እስ?» የእውነትና የሐሰት ብቸኛ መለኪያ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። የእነዚህን ወጣቶች መልስ የመፈለግ

(15). ቀደም ሲል ከተገለጹት ባህርያት አንጻር ክርስቲያናዊ ምግባን ለወጣቶች ለመስጠት አመቺው እንቅስቃሴ የትኛው ነው? እመቺ የሆነውን ቁጥር 1 ያልሆነውን ደግሞ ቁጥር 2 በመስጠት ለይ።

ሀ. ራስን ስለመቀበል ተከታታይ ትምህርቶች መስጠት።
ለ. ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ሰዎች ተከታታይ ታሪኮች መተረክ።
ሐ. ፍቅርን፣ እምነትንና ጋብቻን በተመለከተ ተከታታይ ትምህርት መስጠት።
መ. አካልን መንከባከብ አሳሰፈሳጊ መሆኑን የሚቃወም ተከታታይ ትምህርት መስጠት።
ሠ. የቃሉን ትምህርት በሕይወት ስለመተግበር ተከታታይ ትምህርት ማስተማር።
ረ. ስለ እርስ በእርስ ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተከታታይ ትምህርት ማስተማር።
ሰ. የዘመኑን የባህሪ ጽንሰ ሐሳቦችንና ህብረተሰቡ የሚጠብቅባቸውን ባህርያት እንዲለማመድ በተከታታይ ማስተማር።
ሸ. ወጣቶችና ወላጆች ስተገኙበት የሁለቱን ግንኙነት በተመለከተ በተከታታይ ማስተማር።
ቀ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለማወቅ ተከታታይ ትምህርት መስጠት።
በ. በአእምሮ በእውቀት ማደግ ጥቅም የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ተከታታይ ትምህርት መስጠት።

## የጉልምስና ዘመን

በመጨረሻ የምንመለከተው ዐቢይ የህይወት ዘመን የጉልምስናን ዘመን ነው። ይህ የህይወት ዘመን ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የሆነን ዘመን ይይዛል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የሕፃንነትና የወጣትነት ዘመን «የትምህርት ዘመን» ናቸው። የጉልምስና ዘመን «የገቢ ዘመን» ሲባል ይችላል። የጉልምስና የመጨረሻው ዘመን «የትዝታ ዘመን» ነው፤ ወደኋላ ተመልሶ ሕይወትን የመገምገሚያና የመቃኛ ዘመን ነው፤ ደስታንና ኀዘንን በትዝታ የማስታወሻ ዘመን ነው። ይህ የጉልምስና ዘመን በሦስት የህይወት ዘመኖች ሲከፈል ይችላል፤ በእያንዳንዱ የህይወት ዘመን ላይ የሚታዩ (የሚከሰቱ) ልዩ ባሕርያት አሉ። ይሁን እንጂ በተመሳሳይ የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ ሰዎች አንድ ዐይነት ባሕርይ ያሳያሉ ማለት አይቻልም። አሁን ሰዎች የሚያድጉትም ሆነ የሚለወጡት በፈቃደኝነት በምርጫ እንጂ በአካላዊ ዕድገት ብቻ አይደለም። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ሰዎች አካላዊ ለውጥ ያሳያሉ፤ ሆኖም ለውጡ በሕፃንነትና በወጣትነት ዘመን እንደሚታየው ለውጥ ፈጣን አይደለም።

## ቀዳማይ የጉልምስና ዘመን

ቀዳማይ የጉልምስና ዘመን የሚጀምረው በሃያ ዓመት ግድም ላይ ሲሆን በዚህ የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ ሰዎች የትዳር ጓደኛ ሲፈልጉ፥ የራሳቸውን ኑሮ ሲመሠርቱና ልጅ ሲያሳድጉ ይታያሉ። ጎልማሶች ሥራ መሥራት፥ በሚኖሩበት ኅብረተሰብ ውስጥ ስማቸውን መትከልና ልጅ ማሳደግ ይጀምራሉ።





### *አካላዊ ዕድገት*

ጎልማሳ ማለት «ያደገና የበሰለ» ማለት ነው። ጎልማሳ ሰው አካላዊ ዕድገቱን ከሚጨርስበት የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሷል። በዚህ ዕድሜ ላይ ጽኑ የሚሆነው ጉልበቱ በዳግራይ የጉልምስና ዘመን ላይ መድከም ይጀምራል። ሰዎች ብርቱ ጉልበትንና መልካም ጤንነትን የሚጠይቁ ተግባራትን ለማከናወን ሲነሡ አካላዊ ዕድገታቸው ከመጨረሻው ትልቁ አካላዊ ዕድገት ጋር መድረሉ ነው።

### *አእምሮአዊ ዕድገት*

ብዙ ትምህርት ሲያገኙና ከሕይወትም ብዙ ነገር ሲማሩ የቆዩ ሰዎች ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት ከሚችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። በዚህ ዐይነት ያደጉ ሰዎች የበሰለ አስተሳሰብና የጠራ አመለካከት ይኖራቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ወደፊት ለመሆን የሚፈልጉትን (ለመሥራት የሚያስቡትን ሥራ) ለይተው ይጨርሳሉ። በወጣትነት ዘመን የነበራቸው ጥርጣሬ ሁሉ መስከን ይጀምራል፤ በዚህ ወቅት የረጉና ኀላፊነት የሚሰጣቸው ሰዎች ይሆናሉ።

### *ማኅበራዊ ዕድገት*

በጉልምሰና ዘመን ከቤተሰብ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ትልቅ ቦታ አለው። በቀዳማይ የጉልምስና ዘመን ላይ የሚገኙ ወጣቶች ግንኙነትን የሚመሠርቱት በጽኑ ወዳጅነት ላይ ነው። ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ያድጋል፤ እንዲሁም የጠበቀ ግንኙነትና ወዳጅነት ያስደስታቸዋል። በአንድ ነገር ላይ ለመወሰን የወላጆቻቸው ጥገኛ መሆን አያስፈልጋቸውም፤ ወይም ደግሞ የወላጆቻቸውን ፈቃድ ማግኘት አያሻቸውም። እየበሰሉ ሲሄዱ ለወላጆቻቸው ያላቸው ፍቅርና ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት እየጠበቀ ይሄዳል። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ጎልማሶች ከእነርሱ ጋር ተመሳሳይ ግብና ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት መመሥረት ይፈልጋሉ። ጓደኝነትና ወዳጅነት ከሥራ ቦታ፥ ከቤተክርስቲያን፥ ከጎረቤት ወይም ከትምህርት ቤት ሊገኝ ይችላል። ጎልማሶች ለብቻቸው ተነጥለው ከመኖር ይልቅ ከሚኖሩበት ኅብረተሰብ ጋር መተሳሰር አስፈላጊ መሆኑን ይረዳሉ።

### *መንፈሳዊ ዕድገት*

በሕፃንነትና በወጣትነት ዘመናቸው ሁሉ በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ክርስቲያናዊ ትምህርት እየተማሩ ላደጉ ጎልማሶች ይህ ዕድሜ፥ ቀደም ሲል የተማሩትን ትምህርት በሥራ ላይ የሚያውሉበት ዕድሜ ነው። ለጎልማሶች ይህ ዕድሜ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ዕድሜ ነው። አንዳንድ ጎልማሶች በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ስላላደጉ ወይም በቂ ክርስቲያናዊ ምገባ ስላላገኙ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ዝግጁ አይደሉም። ያም ሆነ ይህ ጎልማሶች ለመንፈሳዊ ነገር ቅድሚያ እንዲሰጡ መበረታታት ያስፈልጋቸዋል። አዲስ ቤተሰብ መሥራች (ወይም አዲስ ጎጆ ወጪ) እንደ

መሆናቸው መጠን የቤተሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ እንዲሁም መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚመግቡበት የተለየ ጊዜ መመደብ እንደ ሚያስፈልጋቸው ሊያውቁ ይገባል። ጎልማሶች ከሚኖሩበት የጥድፊያ ዓለም የተነሣ ከመንፈሳዊ ሕይወት ይልቅ ለምድራዊ ሕይወት ቅድሚያ የሚሰጡበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ይህ እንዳይሆን ኑሮአቸውን በመንፈሳዊ ሕይወት ዙሪያ እንዲያደላድሉ መርዳት ይገባል።

## መካከለኛ የጉልምስና ዘመን

ጎልማሶች ከ35 እስከ 40 ዓመት ላይ ሲደርሱ ወደ ሌላ የህይወት ዘመን ይሸጋገራሉ፤ ይህ የህይወት ዘመን «መካከለኛ የህይወት ዘመን» ተብሎ ይጠራል። በዚህ የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ ጎልማሶች ቀደም ሲል ካሰቡት ነገር ወይም ዓላማ ላይ የደረሱ ሰዎች በመሆናቸው በብዙ ነገሮቻቸው የተደላደሉ ናቸው። ሆኖም ለሌላ አዲስ ሕይወት ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው።

አሁን ልጆች አድገው ትምህርታቸውን ጨርሰዋል፤ በብዙ የሠለጠኑ አገሮች ልጆች ራሳቸውን ችለው ከቤት የሚወጡበት ሰዓት ነው። ልጆቻቸውን ለማስተማርና ለማሳደግ የሚመድቡት ገንዘብ እንዲሁም ጊዜና ጉልበት አሁን አይኖርም። በዚህ ወቅት ወላጆች ባዶነትና ብቸኝነት ሊሰማቸው ይችላል። ምክንያቱም ወልደው ያሳደጉአቸው ልጆች አሁን ካጠገባቸው የሉም። ባልና ሚስት እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት በአዲስ መልክ እንደገና ሊያደራጁት ይገደዱ ይሆናል። በመካከለኛ የጉልምስና ዘመን ላይ የሚገኙ ሰዎች የወደፊት ኑሮአቸው ሊያሳስባቸውና በጥያቄ ሊሞሉ ይችላል። ያሳለፉትን የህይወት ዘይቤ ሙሉ በሙሉ ሊለውጡም ይችላሉ።

በዚህ ዕድሜ ላይ ከሚገኘው ጣፋጭ የህይወት ገጠመኝ ውስጥ አንዱ የልጅ ልጆችን ማየት ነው። የልጅ ልጆች የተለየ በረከት ያመጣሉ፤ ከልጅ ልጆች ጋር ግንኙነት መፍጠር አንድ ራሱን የቻለ አዲስ ገጠመኝ ነው። በዚህ የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ በርካታ ጎልማሶች ወላጆቻቸውን በሞት የሚያጡበት ወቅት ነው። ይህም ራሱን የቻለ አዲስ የህይወት ገጠመኝ በመሆኑ ሌላው የሚታሰብበት ጉዳይ ነው።

### አካላዊ ዕድገት

መካከለኛ የጉልምስና ዘመን በወንዶችም ሆነ በሴቶች ላይ አካላዊ ለውጥ ያስከትላል። ወደ መካከለኛ የጉልምስና ዘመን የሚሸጋገሩ ወንዶች ሰውነታቸው ይሰፋል። ዕድሜ ሲገፋ ጉልበት እየከዳ እንደሚመጣም ያስተውላሉ። ሴቶች ደግሞ የወር አበባቸው ይቆማል። እንደ ወንዶች ሁሉ እነርሱም ሰውነታቸው ሊሰፋ ይችላል፤ እነርሱም የእርጅና ምልክት ለምሳሌ የፀጉር መሸበትና የቆዳ መጨማደድ ሊታይባቸው ይችላል። በአሁኑ ጊዜ በርካታ ሴቶች በወጣትነት ዘመናቸው የነበራቸውን የሰውነት አቋም ለመመለስ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ።





### አእምሮአዊ ዕድገት

በመካከለኛ የጉልምስና ዘመን ላይ የሚገኙ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ያጎለበቱትን አእምሮአዊ ክህሎት በሥራ ላይ የሚያውሉት አሁን ነው። በዚህ የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ ጎልማሶች የሚሰጡት ፍርድ በአብዛኛው ትክክለኛና ታማኝ ነው፤ ይህም በራሳቸው እንዲተማመኑና ብቁ ነኝ እንዲሉ ያደርጋቸዋል። ሰዎች ብዙ ሥራ የሚሠሩትና ፍሬ የሚያፈሩት በዚህ የህይወት ዘመን ነው። ምናልባት በብዙ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የምታያቸው ኀላፊዎች በመካከለኛ የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ ሰዎች ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያት ብዙ ልምድና ችሎታ ስላላቸው ነው።

### ማኅበራዊ ዕድገት

በመካከለኛ የጉልምስና ዘመን፥ በበሰሉ ጎልማሶች ሁሉ ላይ ሌሎችን ሰዎች የመከባከብ ባሕርይ ይታይባቸዋል። የሌሎች ሰዎችን ጉዳይ የራሳቸው ጉዳይ በማድረግ ዕውቀታቸውንና ልምዳቸውን ማካፈል ደስ ይላቸዋል። ሌሎችን ሰዎች በመመገብና በማስተማር ደስታና እርካታ ይሰማቸዋል። በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ጎልማሶች የእነርሱን ሕይወት የባረከውን እውነት ለልጆቻቸው ለማካፈል ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። በሕይወታቸው ዘመን ያዩአቸውን ባሕሎችና ሥርዐቶች እንዳለ ጠብቆ ለማስተላለፍ ጽኑ ምኞት አላቸው።

### መንፈሳዊ ዕድገት

በዚህ የህይወት ዕድሜ ላይ ቁሳዊ በሆኑና ሁለተኛ ደረጃ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ የመጠመድ አዝማሚያ ሊኖር ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ነገሮች የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት እያቀረቀዙ ጊዜአቸውን፥ ጉልበታቸውንና እውነተኛ ራእያቸውን ይነጥቃሉ። በንጻሩም በመካከለኛ የጉልምስና ዘመን ላይ የሚገኙ ሰዎች ጥልቅና ጽኑ እምነት ሊኖራቸው ይችላል።

በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ጎልማሶች አእምሮአዊ ክህሎታቸው እጅግ የዳበረ በመሆኑ፥ ከደረጃቸው ጋር ተስማሚ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ መመገብ ያስፈልጋቸዋል፤ እንዲሁም ትርጉም ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ እንዲኖሩና አገልግሎት እንዲሰጡ ሊበረታቱ ይገባል። በዚህ ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ሰዎች የሚዘጋጀው ትምህርት የሚያመራምር ከመሆኑም በላይ በቂ ዝግጅት የተደረገበት መሆን አለበት። እነዚህ የቤተክርስቲያን አዕማዶች የሚያስፈልጋቸው ትምህርት ጠንካራ ትምህርት ብቻ ሳይሆን የተማሩትን ትምህርት ትርጉም ባለው መንገድ እንዲጠቀሙበት መበረታታት ያሻቸዋል።

## ዳኅራይ የጉልምስና ዘመን

ዳኅራይ የጉልምስና ዘመን የሚጀምረው ከስልሳ እስከ ስልሳ አምስት ባለው የዕድሜ ክልል ነው። በዚህ በመጨረሻው የህይወት ዘመን ላይ የሚገኙ ጎልማሶች፥ ተስፋ የሚያደርጉትትንና የሚያልሙትን ነገር ለመፈጸም የቀራቸው

11. ሀ፣ ሐ፣ ሠ እና ረ

3. ሐ

12. የአንተ መልስ። በጫወታ ጊዜ አካላዊ እና አካላዊ ያልሆነው እንቅስቃሴያቸው ሚዛናዊ መሆኑን ተመልክቻለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆች በአንድ ቡድን ውስጥ አብረው ሲጫወቱ ይታያሉ። ቃላትን አዛብተው ሲናገሩ ይሰማሉ። "አይሆንም" ወይም "ትክክል አይደለም" ሲሉ መስማት የተለመደ ነው። በአንዳንድ ምክንያት የሚያስቅሉ ልጆችም ይታያሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጊዜ በንቃትና በጉጉት ይማራሉ፣ የሚማሩትን እውነት በጥሩ መንፈስ ይቀበላሉ። ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ በሚቀርብላቸው ጥያቄ ጥሩ ምላሽ ሲሰጡ ይታያል።

4. ሀ

13. ሀ፣ ለ፣ መ፣ ሠ እና ረ

5. ሀ

14. የአንተ መልስ። በዚህ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆች ከታናናሾቻቸው ይልቅ ጨዋታ በሚጫወቱበት ጊዜ ጥሩ ክህሎት ያሳያሉ። ጉልበት እንዳላቸውና በሙሉ ልባቸው እንደሚጫወቱ ያስታውቃሉ። ሙከራ ማድረግ፣ የመስክ ጉዞና በአስተማሪያቸው ተመልካችነት በራሳቸው የሚያከናውኑት ሥራዎች በጣም ያስደስታቸዋል። የተማሩትን እውነት ከራሳቸው ሕይወት ጋር ሲያዛምዱና እንደ ክርስቲያን ለመሆን ሲጥሩ ይታያሉ። በስሜታቸው የተረጋጉና ከእኩዮቻቸው ጋር ጥሩ የተጎዳኙ ቢመስሉም ከሌላ ሰው ማበረታታትንና ምክርን የሚፈልጉ ናቸው። ወንዶችና ሴቶች ለየብቻ ተለያይተው ሲቀመጡ ትመለከታለህ።

6. ለ

15. ሀ. 1 ሐ. 1 ሠ. 1 ሰ. 2 ቀ. 1
ለ. 2 መ. 2 ረ. 1 ሸ. 1 በ. 2

7. ሐ

16. ሀ. ሐሰት መ. እውነት ሰ. እውነት በ. ሐሰት
ለ. እውነት ሠ. ሐሰት ሸ. እውነት ተ. እውነት
ሐ. እውነት ረ. ሐሰት ቀ. ሐሰት

8. ሀ. እውነት ሐ. ሐሰት ሠ. እውነት
ለ. ሐሰት መ. እውነት ረ. ሐሰት





# 6 ተማሪ አስተማሪውን ይመስላል

## ትምህርት

አንድ ምሽት ላይ ግርማ ከእርሻው ሲመለስ ፀሐይ እጅግ ደስ ብሏት ነበር። ምክንያቱም በዚያ ምሽት ልጇ አማኑኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ተናግሮ ነበር። ግርማ በዚያ ምሽት የሆነውን ሲያይ እርሱም ደስ አለው። አማኑኤል የሚሰማቸውን ቃላትና ትርጉማቸውን እንዴት ፈጥኖ እንደሚያውቅ ሲያዩ ተገርመዋል። በወላጆቹ እርዳታ አማኑኤል የዕቃዎችን፣ የሰዎችንና የቦታዎችን ስም በትክክል መለየት ቻለ። ባጭር ጊዜ ውስጥ ቃላትን ገጣጥሞ አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን መሥራት ቻለ። ግርማና ፀሐይ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት አማኑኤል ሲናገር ሲሰሙ በጣም ይገረማሉ። ግርማና ፀሐይ ትንሹ ልጃቸው ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው በንግግር እንደሆነ ተረዱ። ሐሳቡን የመግለጽ ችሎታ አለው፤ እርሱን በሚያስደስተው ነገር ላይ መነጋገር በጣም ያስደስተዋል።

«ታዲያ ይህ ምን ያስደንቃል? ምንስ አዲስ ነገር አለው?» ትል ይሆናል። እውነት ነው፤ ሕፃናት በዚህ ዕድሜያቸው የንግግር ችሎታቸውን ያዳብራሉ። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ነጥብ አማኑኤል አሁን እየተናገረው ያለው ቋንቋ የተለየ ቋንቋ ሳይሆን ቤተሰቦቹ ሁሉ የሚናገሩትን ቋንቋ ነው። ቤተሰቦቹ የሚወዱትን ምግብ መመገብ ችሎአል፤ እንዲሁም ቤተሰቦቹ ያሉበት ዓለም የሚኖረውን ሕይወት እርሱም መኖር ጀምሮአል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለዚህ ጥያቄ ልንሰጠው የምንችለው ምክንያታዊ መልስ፥ ከቤተሰቦቹ ተጽዕኖ የተነሣ ነው፤ ከቤተሰቦቹ ጋር የቅርብ ግንኙነት ስላለው አመለካከቱ፥ ፍላጎቱና ባሕሪው የቤተሰቦቹን ሊመስል ችሎአል።

ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ አለ፦ «ተማሪ ትምህርቱን በደንብ ከተማረ እንደ አስተማሪው ይሆናል» (ሉቃ. 6፥40)። ይህም ማለት ተማሪ ከአስተማሪው ሕይወት ብዙ ይወስዳል። እንግዲህ መደበኛ ያልሆነ ክርስቲያናዊ ምገባ፥ ክርስቲያናዊ ዕድገትን ለማምጣት ትልቅ ሚና አለው። በዚህ ትምህርት ውስጥ መደበኛ ስላልሆነ ክርስቲያናዊ ምገባ ባሕርይ ትማራለህ። ከሌሎች ጋር በመነጋገርና (በመወያየትና በመጫወት) አብሮ በመዋል እንዴት መማር እንደሚቻል ትማራለህ። ከዚህ በተጨማሪ በክርስቲያናዊ ምገባ ውስጥ ትልቅ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ትገነዘባለህ።